# ማደጎ 2

ትንሽ... እርፍጃለሁ። በወጣሁበት ሰዓት፡ ነውጠኛ ሰው አጋጠመኝ፡ እና በጣም፡ በጣም ነውጠኞች፡ መጥፎዎች ናቸው። ከሚቺጋን ጀምሬ እየነዳሁ፡ መንገድ ላይ ትራፊኮች አስቆሙኝ፡ እና እጅግ፡ መጥፎዎች ሆኑብኝ። አሁን፡ መልካም ነው፡ አሁን—ነገሩ ተረጋግቷል፡ ችግር የለውም። ጌታ ሲመጣ፡ ሁሉም ይረጋጋል፡ አይደል'ዴ? ኦህ፡ እሱ መ—መልካም ነው፤ ምሕረቱ እና መልካምነቱ፣ ለእኛ ያለው ትርጉም ስታስቡት፡ ምስጋናው እንዴት ድንቅ ነው።

እሺ፡ ከኤፌሶን መጽሐፍ ፊተኞቹ ሶስት ምዕራፎችን እንማራለን፡ ብለን ነበር። የመጀመርያ ሶስት ቃላት፡ ወይም በዚያ ውስጥ ያሉ የመጀመርያ ሶስት **ነገሮች** አይተናል። ብዙ ርቀን ግን አልሄድንም፡ ምናልባት ዛሬ ማታ ትንሽ ገፋ እናደርገዋለን። አሁን፡ ስለራሴ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር አለመሆኔን፡ ከቲኦሎጂ ትምህርት እጅግ የራቀ ሰው መሆኔን፡ መናገር እፈልጋለሁ፡ ጌታን ግን—እወዳለሁ፡ እሱን ማገልገል እወዳለሁ... [አንድ ወንድም ለወንድም ብራንሃም ተናገረው—አርታዒ።]

ከመቀጠላችን በፊት፡ በሎይስቪል ሆስፒታል፡ ድንገተኛ ክፍል፡ የገባች ህጻን ልጅ፡ እንዳለች፡ አንድ ግለሰብ አሳስቧል፡ እስፔሻሊስቶች ተስፋ ቆርጠውባታል፡ በሞት አፋፋ ላይ ትገኛለችና፡ ለህጻኗ ጸልዩ ተብለናል። እንደ ክርስትያኖች፡ አንገታችንን፡ ለጸሎት ዝቅ ማድረግ፡ ግዴታችን ነው።

ቸሩ ጌታችን ሆይ፡ ግዴታ ብቻ ሳይሆን፡ መታደልም ነውና፡ እንደ ቸርች—አንገታችን ዝቅ ማድረግ መሻታችን ነውና፡ ተጠርቶ-እንደወጣ፡ እንደ አማኝ ህዝብ፡ ዛሬ ምሽት ቃልህን ማስተማር እንችል ዘንድ፡ ቦታ ቦታችንን አስይዘህ፡ የክርስቶስ አካል አባላት እንደመሆናችን መጠን፡ በአንድነት በየሰፍራችን እንድንተጋ አድርገን።

2 ደግሞም ፈጥነን በእግዚአብሔር ፊት እንድንቀርብ ተጠይቀናል። አባቶች የሆንን ሁላችንም፡ ከልብ በመሰበር እና በምሬት፡ ህጻኗ ልጄ ብትሆን ኖሮስ ብለን እናስብ፡ ቸርቾች ሁሉ እንዲጸልዩልን በጠየቅናቸው ነበር። አሁንም የአንድ አባት ልብ፡ በምሬት ህመም ላይ ነው። ጌታ ሆይ፣ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ አሁን ወደዚያ አባት ልብ ይምጣ። ጥርጣሬውን ሁሉ እና፡ ህመሙ ሁሉ አስወግድለት፡ መለኮታዊ ተልዕኮህ በቤተ ክርስቲያንህና በሕዝብህ ሲፈጸም አንተ አምላክ መሆንህን በፊትህም ሊቆም የሚችል በሽታ እንደማይኖር አረጋግጥለት።

3 ሳምንት ሙሉ፡ ሰንጸልይ፡ ካለፈው እሁድ ጀምሬ በእነዚህ ጉዳዮች እና የጸሎት አቅጣጫዎች ላይ ሳስብ ነበር። ከዓለም ጋር ሰንተያይ የጦር ዕቃችን ደካማ ነው፡ ትንሿ ወንጭፋችን በእምነት ጣቶች ውስጥ ስትያዝ ግን ብርቱ ናት። ጌታ ሆይ፡ ጸሎታችን ማደርያህ ይድረስ፡ በሕጻኗ ላይ የተንጠለጠለ የሞት ጥላ፣ ጨለማ፤ ጭጋግ፡ ከብላቴናዋ፡ ከሕጻኗ ወይም ጨቅላ ልጅ፡ ጨቅላዋ ከተኛችበት አልጋ፡ አሁን ይራቅ፡ አሁን ይሰበር። የእግዚአብሔር የመገኘቱ ታላቅ ብርሃን በላይዋ ላይ ይብራ። ጤነኛ ልጅ ሆና ከሆስፒታል ትመለስ።

4 ጌታ ሆይ፡ ከወንዙ ማዶ ውብ አገር፡ ወዳጆቻችን እንደሚጠብቁን እናውቃለን። ይሁን እንጂ ልጆቻችንን እንወዳቸዋለንና። ጌታ ሆይ፡ ስለ ክብርህ የብላቴናዋ ህይወት ትታደግ ዘንድ፡ እንማጸንሃለን። እኛ፡ እንደ ቤተክርትያንህ፡ ያንን ሞት እንገሰጸዋለን፦ “ወደዛ ራቅ ሂድ። ህይወቷን ለእግዚአብሄር መንግስት ዋጅተነዋልና፡ ህጻኗን መውሰድ አትችልም፡” እንለዋለን። ጌታ ሆይ፡ እንደመራናቸው ወደ ምልክቱ መድረስ ይችሉ ዘንድ፡ እነዚህን ፈጽምልን፡ በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

5 አምነናል? ክርስቲያን ባልሆን ኖሮ ምን ልሆን እንደምችል አላውቅም። እኔ ከዚህ በላይ እዚህ መቆየት አልመኝም። ሌሎች እንዲድኑ ካልሆነ በቀር፡ ይሄ ነው የምለው፡ የምኖርለት ነገር የለኝም።

6 ዛሬ ማታ፡ ባለፈው የተማርነውን ትምህርት ዳራው በመከለስ እንጀምራለን። ምክንያቱ፡ ዛሬ ማታ ከቻልኩ፡ ምዕራፉን በሙሉ፡ ለማንበብ እሞክራለሁ። ስለዚህ ምናልባት ካላስቸገርኳችሁ፡ ቤተ ክርስትያን እንድታየው የፈለግኩት ነገር ላይ ለመድረስ፡ እሁድ ሁለቱንም ክፍለ ጊዜ እሁድ ጠዋት እና ማታ ለመጠቀም እሞክራለሁ። ኦህ፡ ርስትህን ማግኘት ድንቅ ነገር ነው! የሚሰራውን ጠንቅቆ ሳያውቅ ስራውን የሚያከናውን ሰው የለምና።

7 ለምሳሌ ያክል... ቀዶ ጥገና ሊደረግልግ እየሄድክ ነው፡ ቀዶ ጥገና አድርጎ የማያውቅ... ከትምህርት ቤት አሁን የወጣ ወጣት ቢመጣባችሁስ። ወጣት ነው፡ ቆንጆ ነው፡ ጸጉሩ ለጥ ያለ የተበጠረ፡ ሽክ ብሏል፡ እጅግ የሚያምር፡ ወዘተ። መጥቶ “ስለቶቹን በትክክል ሞርጃለሁ፣ መሳርያው በሙሉ ስተሪላይዝ አድርጌአለሁ፡” ቢላችሁም። የሚሰማችሁ እንግዳ ስሜት መኖሩ የማይቀር ነው። እንደ’ኔ ከመታረዴ በፊት፡ ብዙ የቀዶ ጥገና ልምድ ያለው ሽማግሌ ዶክተር ቢሰራልኝ እመርጣለሁ። እ—አዲስ ተመራቂ ያልሆነ ሰው ባውቅ ይሻለኛል፡ ልምድ ያለው ሰው እመርጣለሁ።

8 ዛሬም በዚህ ረገድ፡ እጅግ ጥሩ ልምድ እንዳለው አውቄ የምጠራው፡ መንፈስ ቅዱስን ነው። ከእግዚአብሄር ዘንድ የሆነ ታላቅ ሐኪም እና አስተማሪ እሱ ነው።

9 አሁንም ከእሁዱ ስብከት፡ ለዛሬ ማታ የመልዕክቴን ድህረ-ዳራውን አስቀምጣለሁ፡ ይህም፡ መንፈስ እንደመራው ስለሚናገር፡ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ የነበረ፡ ሳሙኤልን ነቀው፡ የጌታን ቃል የያዘውን ሰው፡ ሳሙኤልን ነቀው፡ የቂስን ልጅ ሳኦልን መምረጣቸው ነው። ሲያስጠነቅቃቸውም፡ እንዲህ ብሏቸው ነበር፦ “በጌታ ስም ተናግሬአችሁ ከተፈጸመው በቀር ሌላ አላልኳችሁምና፡ ይህን አስቡ። በመካከላችሁ ሳለሁ በማይረባ ረብ አልተመላለስኩም። ስለ ሐጥያት የሚኰንነኝ ሰውም የለም።”

ኢየሱስም ሲናገር “በኃጢአት እኔን የሚኮንን ማን ነው ብሏል?” አያችሁ?

10 እንደገናም ሳሙኤል፡ እንዲህ አላቸው፦ “በእናንተ ዘንድ በመጣሁ ጊዜ ስለ ገንዘብ እና ረብ አልጠየቅኳችሁም። ከእናንተም አንዳች አልወሰድኩም። የነገርኳችሁ ሁሉ ከእግዚአብሄር አፍ ወደ እናንተ ያመጣሁት ሁሉ ግን፡ ለመልካማችሁ ነበር አላቸው።”

11 ህዝቡም ሁሉ መሰከሩ፦ “አዎን። ይህ ሁሉ ትክክል ነው፡ ይሁን እንጂ ንጉስ እንዲኖረን እንፈልጋለን። እንደሌሎቹ አሕዛብ መሆን እንፈልጋለን አሉ።”

12 አሁን፡ ዛሬም፡ ቅዱስ ቃል ተቆርሶልናል… የኤፌሶን መጽሐፍ፡ በአዲሱ ኪዳን መጽሐፈ ኢያሱ ነው። “ስለ ድል ነሺዎች” እየተቆረሠ ስፍራ ስፍራውን እየያዘ ይገኛል። አሁን ዋናውን ለማግኘት፡ ማንበብ ከመጀመርያችን በፊት፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ዳራውን ብቻ እናያለን፡ ከቁጥር 3 እንጀምር። እንግዲህ፡ ባለፈው እሁድ ምሽት እንዳየነው… በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን መጻተኞች እና ተጓዥ ብቻ ስለነበሩ፡ እግዚአብሔር የዕረፍት ምድር ቃል ኪዳን እንደገባላቸው አይተናል። በሰው አገርም ነበሩና፡ እግዚአብሄርም ለአብርሃም የሚቀመጥባትን እንደሚሰጠው ቃል ገባለት… ዘሩ ለአራት መቶ ዓመታት በሌላ ሕዝብ ምድር እንደሚቀመጡ፡ እና መከራ እንደሚደርስባቸው፡ ነገር ግን በጽኑ ክንዱ አውጥቶ ወተት እና ማር ወደምታፈስው መልካሚቱ ምድር እንደሚወስዳቸው ቃል ገብቶለታል።

13 ስለዚህ፡ የተስፋቃሉ የሚፈጸምበት ዘመን፡ በደረሰ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ወደ መልካሚቱ ምድር የሚያደርሳቸው ሰው አስነሳላቸው። ያ ሰው ማን እንደነበረ… እስኪ ሰንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ? ሙሴ። ይህ ማለት፡ እኛን ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማድረስ የተሰጠ፡ ክርስቶስ፡ እውነተኛ እና እውነተኛ ጥላው ነበር። እኛም አሁን ተሰፋ ቃል አለን፡ ይህም መንፈሳዊ የዕረፍት ተስፋ ቃል ነው፡ የእነሱ እረፍት ግን፡ ስጋዊ ነበር። በዚህም ምክንያት እንዲህ ብለው የሚመኩባት ምድር ውስጥ ደረሱ፦ “ይህች መሬታችን ናት፡ ከእንግዲህ አርፈናል፡ ተቅበዝባዦች አይደለንም፡ ይቺ ምድራችን ናት፣ እዚህ አርፈናል። የበቆሎቻችንን፣ የወይን እርሻዎቻችንን እንዘራለን፣ ከወይኑ እርሻችን እንበላለን። ከዚያም እኛ ስናልፍ፡ ለልጆቻችን እናወርሳታለን።”

14 ኦህ፡ እንደነ ናኦሚ እና ሩት፣ ቦኤዝ የመሳሰሉ ሰዎች፡ የርስት ህግ ያለባት ምድር ሄደን፡ በእስራኤል አንድ ሰው፡ የወንድሙ የሆነውን፡ ሁሉን እንዴት እንደሚያስመልስ… የጠፋበትን ነገር ሁሉ በዋርሳ እንዴት እንደሚቤዥለት። ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! ይህ ምዕራፍ ከገባንበት፡ ከሳምንት ወደ ሳምንት ከሳምንት ወደ ሳምንት ይቀጣላል እንጂ፡ እናቆመውም። መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ፡ ወደዚች አንዲት ምዕራፍ መጠቅለል እንችላለን።

15 እንደው፡ በቃ፡ ይሄንን ሳጠና ደስ ይለኛል። ያኔ ጥናት ላይ፡ ከአንዲት መጽሐፍ ሳንወጣ፡ ከአንድ ዓመት ከግማሽ ድረስ እናጠናው ነበር። ሳንላቀቀው።

16 እንግዲህ፡ ርስት ማለት፡ እጅግ ታላቅ ነገር ነው፡ በዚያ ምድር የነበረው የርስት አወራረስ ስርዓት ርስትን የሚያስመልስ ሰው የቀረበ ዋርሳ ከሆነ በቀር አይቻልም። አሁን ለእናንተ ለእናቶች፡ ባለፈው ማታ ላይ ከዳሰስኩት ነገር፡ ምልክትን ልጣልላችሁ። እስኪ ስለሞቱ ወዳጆቻችሁ ጸልያችሁ የምታውቁ፡ ሰንቶች አላችሁ? በጣም ጥሩ። አሁንም ይሄውላችሁ፡ አያችሁ፡ “ርስታችሁ።” አያችሁ?

17 ጳውሎስ ሮማዊውን ሰው፦ “በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እመንና፡ አንተ እና ቤትህ ትድናላችሁ፡” ብሎታል። አንተ ለራስህ እድናለሁ የሚል በቂ እምነት ካለህ፡ እመን ብቻ፡ ወንዱ ወይም፡ ሴቷ ምን ያህል የወደቁ ቢሆኑም እንኳ፡

እንዲሁ ይድናሉ። እግዚአብሄር፡ ያደርገዋልና! ምንም ያህል ሆስፒታል ላይ፡ በሞት አፋፍ ደርሰው፡ በጀርባቸው ቢያስተኛቸውም'ኳ፡ ይድናሉ። ስለ ርስት! እግዚአብሄር ቃል ገብቷልና። ኦህ! ኢሳያስ ሲናገር፡ "በዚያም ይገቡባታል፡" "ሁሉም እስከነ ልጆቻቸው። በቅዱስ ተራራዬ አይጠፉም አይጎዱም፡ ይላል ጌታ" ብሏል።

18 ኦህ፡ ዛሬ ማታ እናንተን ለማድረስ የያዝኳት፡ አንድ ስፍራ አለችኝ። በልቤ ውስጥ ትቀጣጠላለች፡ ከሷ መጥተናል ወደሷ እንመለሳለን።

19 አሁን ግን፡ ስንቀጥል። እስራኤልን ከዚያ ምድር አውጥቶ ወደ ምድሪቱ ያመጣቸው ታላቁ ተአምር ሰሪው ሙሴ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር አድርሶ፡ ርስታቸውን እንዳልሰጣቸው፡ አስተውላችሁታል ወይ? ርስታቸውን አልሰጣቸውም፡ ሙሴ ወደ ምድሪቱ መራቸው፡ ኢያሱ ግን ምድሪቱን ለህዝቡ አከፋፈላቸው። ልክ ነው? ክርስቶስም ቤተ ክርስትያን ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ ወደ ርስታቸው አደረሳቸው፣ ዮርዳኖስን እንዲያሻግራቸው፡ ብቻ ተሰጣቸው፡ የቤተ ክርስትያን ስርዓት ቦታ ቦታዉን ያሰያዘ ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። ለእያንዳንዱ ሰው፡ ስጦታን፡ ስፍራን፡ እና ሐላፊነትን እየሰጠ፡ የዛሬው ኢያሱ ቤተ ክርስትያንን ስርዓት ቦታ ቦታውን አስያዘ። እሱም ክርስቶስ ባዳነው በውስጠኛው ሰው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የሚናገር የእግዚአብሄር ድምጽ ነው። በተወሰነ መልኩ ገብቷችኋል? አሁን፡ በቀጥታ ወደ ኤፌሶን መጽሐፍ እንገባለን። አሁንም፡ በተመሳሳይ መልኩ፡ ቤተ ክርስትያን ቦታ ቦታቸውን አስይዟቸዋል። ኢያሱ፡ በተፈጥሯዊው ምድር ላይ አደረሳቸው። መንፈስ ቅዱስ ግን፡ ቤተክርስቲያንን፡ እያንዳንዳቸው፡ በየተጠሩባት ምድር፡ በየተመደቡበት፣ በየርስታቸው እያስቀመጣቸው ይገኛል።

20 አሁን፡ የደብዳቤውን አጻጻፍ፡ አስቀድሞ፡ "ጳውሎስ… " በማለት ይጀምረዋል፡ ይህም፡ ለጳውሎስ የተገለጡለት ምስጢራቶች ሁሉ እግዚአብሔር ለጳውሎስ በሰጠው በመንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ መገለጥ እንጂ፡ ከትምህርት ቤት፡ ወይም ከማናቸውም የሰነ መለኮት ምሁራን እንዳልተገለጠለት፡ ከአፍታ ቆይታ በኋላ እናየዋለን። እሱም ሲናገር፡ ከዓለም ምስረታ በፊት፡ ተሰውሮ የነበረው የእግዚአብሄርን ምስጢር፡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ተገልጦልኛል ይላል። መንፈስ ቅዱስም በሕዝቡ መካከል ለቸርች ሕግ እና አካሄድ በማበጀት እያንዳንዱን ሰው በሥርዓት ቦታ ቦታውን አስይዟል።

21 እንግዲህ እዚጋ ጳውሎስ ለህዝቡ መናገር የጀመረው፡ ሊረዱት የሚገባ ቀዳሚው ነገር… ማለት አስታውሱ፡ ይህ በውጭ ላሉት ሳይሆን፡ ለቤተ ክርስትያን ነው። ለእሱ የእንቆቅልሽ ምስጢር ነው፣ በጭራሽ ሊረዳው አይችልም፣ ጭንቅላቱ ውስጥ ይገባል፣ ቢሆንም ከሌላው እውቀት በተለየ መልኩ አያውቀውም። ለቤተክርስቲያን፡ ግን፡ በዓለት ውስጥ እንዳለ ማር፣ የማይነገር ደስታ፣ የተባረከ ዋስትና፣ የነፍስ መልህቅ፣ ተስፋችን እና ማቆያችን፣ የዘመናት አለት፣ ኦህ፣ መልካም የሆነው ሁሉ ነው። ሰማይና ምድር ያልፋሉና፡ የእግዚአብሔር ቃል ግን አያልፍም።

22 ከከነዓን ውጭ ያለ ሰው ስለ ከነዓን ምንም አያውቅም፡ አሁንም በመንከራተት ላይ ነው። ጥሩ ሰው አይደለም እያልኩ አይደለም፡ እኔ

ይሄን አላልኩም። በግብጽ ውስጥ የነበረው ሰው መልካም ሰው አይደለም አላልኩም፡ ነገር ግን... ወደዚህ ርሰት እስኪገባ ድረሰ።

23 ይህ ርሰትም፡ ማለት፡ ለቤተ ክርስትያን የተገባላት የተሰፋው ቃል መንፈሳዊ ምድር ነው እንጂ፣ ተፈጥሯዊ ምድር አይደለም፣ ይህም የንጉስ ክሃናት፣ ቅዱስ ህዝብ መሆናችን ነው። እኛም የንጉሥ ክህነት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ልዩ ሕዝብ፣ የተጠራን፣ የተመረጥን፣ በምርጫ የተለየን፣ የተቀመጥን ስንሆን፣ ዓለም ሁሉ በውጭው ሞቷል። እኛ ግን የምንመራው በመንፈስ ነው። በመንፈስ እንጂ በሰው አይመሩም፡ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በእግዚአብሔር መንፈስ ይመራሉ።

24 አሁን ይህ ሁሉ የሚጠቀለለው፡ ፍቅር ላይ ነው። ብዙ ጊዜ ይሄን ለማስተማር ተሞክሯል፡ ያለጥርጥር የሰነመለኩት ምሁራን የሆኑ ሰዎች ከእኔ በላይ ዘልቀው ይህን አስተምረዋል። እኔ ግን ወደ እናንተ ማድረስ የፈለግኩት ይህ ነው፦ በክርስቶስ የሆነ፣ መንፈስ ቅዱስም የተሞላ ሰው፡ ሌላ ሰው ሲያጠፋ ይታገሳል፡ ትዕግስተኛ፣ ጨዋ፣ ታጋሽ፣ ጣፋጭ፣ ትሑት፣ ታማኝ፣ በመንፈስ የተሞላ ነው፤ ሁልጊዜ አዎንታዊ እንጂ፡ አሉታዊ ያልሆነ፡ የተለየ ሰው ነው።

25 አንድ ሰው "ድሮ አግኝተነዋል። እኛ ሜቶዲስቶች፡ ጩኸት በጩኸን ጊዜ፡ ያኔ ድሮ፡ ገብተናል። ኦህ፡ በጩኸን ጊዜ፡ ምድሪቱ ውስጥ ገብተናል።" እንደሚለው አይደለም፡ በርግጥ መልካም ጥሩ ነው፡ በዚህም እምናለሁ።

26 ጴንጤቆስጤዎች ልሳን እየተናገሩ ይመጡና፦ "የሚያገኛት፡ በልሳን የጸለየ ሰው ያገኛታል፡" ይላሉ። በዚህም፡ አምናለሁ። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ ገና አልደረሱም፡ እያችሁ። ተረዳችሁት? እነዚህ ሰዎች...

27 አሁን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ወደ ተሰወረውና በመጨረሻው ዘመን ለእግዚአብሔር ልጆች ወደ ተገለጠው ወደዚህ ታላቅ ሰውር ምሥጢር እየመጣን ነው። የእግዚአብሄር ልጆች እንደተገለጡ፡ ይህም እውነት እንደሆነ ታምናላችሁ? የትም ከመሄዳችን በፊት፣ አንድ ደቂቃ ብቻ ሮሜ ሰዎች 8ኛው ምዕራፍ እንክፈትና፣ አንድ ነገር ላንብብላችሁ። ይህ እኔ ወደምናገረው ነገር እየመጣ እንደሆነ መርምሩ። አሁን ከሮሜ ሰዎች 8፡ ቁጥር 19 እንከፍታለን—ሮሜ ሰዎች 8ተኛው ምዕራፍ፦

> የፍጥረት... **ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች** መገለጥ **ይጠባበቃልና**።

28 ፍጥረት ሁሉ፡ መገለጥ በናፍቆት እየተጠባበቀ ነው። እያችሁ፡ መገለጥ! መገለጥ ምንድነው? መታወቅ ነው!

29 ዓለሙን በሙሉ። ማዶ ያሉት መሐመዳውያን በሙሉ፡ እየተጠባበቁ ናቸው። ባጠቃላይ፡ በሁሉም ሰፍራ፡ እየተጠባበቁት ይገኛሉ። "ያ ህዝብ ወዴት ነው? " ሁሉንም እየነው... ታላቁ አውሎ ነፋስን እየን፣ ነጎድጓዶች እና መብረቅ አየን፣ ደሙንም ዘይቱንም አየን፣ ሌላው ነገር ሁሉ አይተነዋል፣ ነብዪው መጎናጸፊያውን ፊቱ ላይ ሸፍኖ እንዲወጣ ያስቻለችው "እነሆኝ፡ ጌታ ሆይ፡" ያሰባለችው፡ ትንሿን ድምፅ ግን መሰማት ተሰኖናል። እያችሁ?

30 ፍጥረት ሁሉ በታላቅ ምጥ ውስጥ ሆኖ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ እየጠበቀ ይገኛል። አሁን በመጀመርያ፡ ጳውሎስ ቤተ ክርስትያንን

መገኘት ባለባት በትክክለኛ ቦታ ያስቀምጣል። ዳራውን ለማግኘት፣ እንደገና እናንብበው፦

**በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፡ በኤፌሶን ላሉት** (“ቅዱሳን” ለሆኑት) **ቅዱሳን፡ በክርስቶስ ኢየሱስም... ላሉት ምእመናን፤**

31 ስለዚህ፡ ተማሪዎች እንዳይረሱ፡ ወደ ክርስቶስ የምንገባው እንዴት ነው? ወደ ክርስቶስ ለመግባት የቤተ ክርስትያን አባላት መሆን ያስፈልጋልን? ወደ ክርስቶስ ለመግባት ሞያተኞች መሆን ያስፈልገናልን? ወደ ክርስቶስ ለመግባት በጥልቅ ውሃ መዘፈቅ ይገባናልን? ወደ ክርስቶስ የምንገባው እንዴት ነው? አንደኛ ቆሮንቶስ፡ 12ኛ ምዕራፍ፡ “በአንዱ መንፈስ፡” ሲል፡ በትልቁ ፊደል ኤስ-ፒ-አይ-አር-አይ-ቲ፡ መንፈስ ቅዱስን ነው፣ “ሁላችንም ወደ ተሰፋይቱ ምድር ተጠምቀናል።”

32 በተሰፋ ቃል ምድር፡ በተሰፋይቱ ምድር የሚገኝ ነገር ሁሉ የኛ ነው። አየህ፡ ወንድም ኮሊንስ? አያችሁ፡ በተሰፋይቱ ምድር ያለ ነገር በሙሉ! እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግሮ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር በደረሰ ጊዜ፡ ስለ ሁሉም ነገር ተዋግቷል!

33 አሁን አስተውሉ፣ በተሰፋይቱ ምድር ውስጥ፡ ከበሽታ ነፃ ነህ ማለት አይደለም፣ ከችግር ነፃ ነህ ማለት አይደለም። መልዕክቱ ግን እንደሚከተለው ነው (ኦህ! ይህ ነገር በደንብ ተረዱት።)፡ ይህም፡ ሁሉም የእናንተ ነው ይላል! ተነስ እና ውረስ! አያችሁ? እንግዲህ...

34 ይህን፡ አስታውሱ፡ በእስራኤል ወገን ሰው የሚሞተው፡ በሰፈራቸው ሐጥያት ሲገባ ብቻ ነበር። ድላችንን—ውድቅ ከሚሆንበት ብቸኛው መንገድ፡ ሐጥያት ወደ ሰፈራችን ሲገባ፡ እና በአንዱ ወገን ክፍተት ሲኖርብን ብቻ ነው። አካን ወርቅ እና የባቢሎንን ልብስ በሰረቀ ጊዜ ኃጢአት በሰፈር ውስጥ ገባ፤ ጦርነቱም ተበላሸ።

35 ይህንን ያዙልኝ—ዛሬ ማታ ይህ ቤተ ክርስትያን፡ እነኚህ ሰዎች፡ በእግዚአብሔር ተሰፋ ቃል ፍጹምነት፡ በመንፈስ እየተጓዙ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ፍጹማን ቢሆኑ፡ አለ የሚባል በሽታ ወይም መከራ ወይም ማንኛውንም ነገር፣ በአገሪቱ ውስጥ አሉ የሚባሉ እያንዳንዳቸው ጆይ ሉዊሶች፡ እና እምነት አልባ ሰዎች ሁሉ፡ እስከነ ክህደታቸው ጋር፣ ህመምና መከራ ይዘው በር ድረስ ቢመጡ፡ ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ሆነው መውጣታቸው አይቀርም። አዎን፡ ጌታዬ። እግዚአብሄር ቃል ገብቶልናል፡ ቃሉን የሚከለክለው የአለማመን ሐጢአት ብቻ ነው። ይህች ትንሽ ሐጢአት ምን እንደሆነች፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንመለከታታለን። ስለዚህ፦

**... በክርስቶስ ኢየሱስ** ላሉት፦

**ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከ... ጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጸጋና፡ ሰላም፡** ለእናንተ **ይሁን።**

**በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡ በ—በ ክርስቶስ፡**

36 በክርስቶስ ስንሆን፡ መንፈሳዊ በረከት እናገኛለን። ከክርስቶስ ውጭ ግን፡ ስሜቶች ብቻ። በክርስቶስ ትክክለኛ በረከት አለን። አስመሳይ-እምነት የለም፣ ለምድ-እንለብስም፡ ያልሆነውን አንሆንም። ነገር ግን በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ሳትገባ፡ ገብቻለሁ ብትል፡ ኃጢአትህ እራሱ ያጠምድሃል። እና፡ ከሁሉ በፊት፡ በዓለም እንደምንለው—እራስህን ቂል፡ እና ልስን ግድግዳ ሆነህ ታገኘዋለህ። ነኝ ብለህ የምታወራውን ነገር ገና እንዳልያዝከው ትደርስበታለህ። በክርስቶስ ኢየሱስ ስትሆን ግን፡ ሰማያዊ ሰላም፣ ሰማያዊ በረከት፣ ሰማያዊ መንፈስ፣ ሁሉም ነገር የአንተ ይሆናል። በተስፋይቱ ምድር ውስጥ ትሆናለህ ሁሉም የአንተ ነው። አሜን። እንዴት ድንቅ ነው! ኦህ፡ እሺ እንቀጥል፤

**በእርሱ** እንደ **መረጠን**...

37 ቤተክርስትያን እጅግ የምትሰተው፡ እዚህ ጋር ነው።

**በእርሱ ዘንድ** እንደ **መረጠን...** (በማን ዘንድ? ) በክርስቶስ ዘንድ።

38 ወደ ኋላ መለስ ብለን በዘፍጥረት እና በራእይ ላይ፡ እንዲህ እናገኛለን፣ ራእይ 17:8 ላይ፣ ዓለም ሳይፈጠር በፊት በክርስቶስ እንደመረጠን እናያለን። ስለዚህ፡ ይህ ቃል... ቀጣዩን ቃል ላንብበው፡-

... **ዓለም ሳይፈጠር፡ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ...**

**አስቀድሞ ወስነን...**

39 አሁን "አስቀድሞ ወስነን" በሚለው ቃል ቆም እላለሁ። ተከታተሉኝ፡ **አስቀድሞ መወሰን**፡ "ወንድም ነቪሌን እመርጠዋለሁ፡ ወንድም ቢለርን ግን አ—አ—አ—አ—አልመርጠውም ማለት አይደለም።" እንዲህ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሄር በቀደመው እውቀቱ ማን ትክክል ይሆናል ማን ይሳሳታል ማወቁ ነው። ስለዚህ፡ በቀደመው እውቀቱ፡ እግዚአብሄር ምን ሊያደርግ እንዳለው በማወቁ፣ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲሠራ አስቀድሞ በማወቁ አስቀድሞ ወሰኗል፣ ይህም፡ በዘመን ፍጻሜ፡ ነገር ሁሉ በአንድ ለመጠቅለል ነው፡ እርሱም በክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

40 እዚህ ላይ ትንሽ ምሳሌ ልሰጣችሁ። እጅግ ይጠቅማል። በቀደም ለት ማታ፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን፡ ጥቂቱን ነክቼዋለሁ ወይም ጠቅሼዋለሁ፡ በዘፍጥረት፡ 1ኛው ምዕራፍ፡ 1:26 ላይ፣ "ጌታ አምላክ፡" እግዚአብሄር ሰሙን ሲጠራ፡ ኤል፣ ኤላህ፣ ኤሎሂም በሚል ቃል ነበር፣ ይህ ማለት "ብቻውን-የሚኖረው" ማለት ነው። ከእርሱ በቀር ህያው ሆኖ የኖረ አልነበረም። ንፋስ አልነበረም፣ ብርሃን አልነበረም፣ ከዋክብቶች አልነበሩም፣ ዓለማትም አልነበሩም፣ ወይም ሌላ ነገር አልነበረም። አምላክ፣ እና እና አምላክ ብቻውን ነበር፡ ኤል፣ ኤላህ፣ ኤሎሂም። በዚያም፡ ብዙ ነገሮችን አበጀ።

41 በዛው ውስጥ እርሱን የሚገልጹ ብዙ መገለጫዎች... ማለት በኤል፣ ኤላህ፣ ኤሎሂም ውስጥ መገለጫዎች ነበሩት ወይም... **መገለጫ** ታውቃላችሁ፡ ወይም "ተፈጥሮ" ነበረው፡ ብዬ ላስቀምጠው። ይህም እውነት ታናናሾች ያውቁታል፡ እኔም በዚህ መልኩ ከሚያውቁት ከታናናሾቹ መካከል አንዱ ነኝ። በውስጡ አባት የመሆን ተፈጥሮ በራሱ ነበረው፣ ብቻውን-የሚኖር

ስለሆነ ግን፡ አባት የሚያሰይመው አንዳች አልነበረም። እናም፡ አሁን፡ በውስጡ ግን የሆነ ነገር አለ፡ ይህም አምላክነቱ ነው፤ አምላክ ማለት የሚመለክ ነገር ማለት ነው፤ እርሱ ግን ብቻውን-የሚኖር፣ ኤል፣ ኤላህ፣ ኤሎሂም ስለነበረ፣ የሚያመልከው አንዳችም አለነበረም። በውስጡ፡ አዳኝነት ነብረው፣ መዳን የሚያስፈልገው የጠፋ ነገር ግን አንድም አልነበረም። አያችሁ? በውስጡ፡ ፈዋሽነት ነበር፡ አያችሁ፡ ፈውስ የሚያስፈልገው የታመመ ሰው ግን የለም፡ የሚታመም አልነበረም። አሁንስ ሐሳቡን አገኛታችሁታልን? ስለዚህ ዛሬ የሆነውን ነገር እንዲሆን ያስደረገው ተፈጥሮው ነው፡ መገለጫዎቹ ናቸው።

42 አንዳንድ ሰዎች፦ “እሺ፡ ለምን ከጅምሩ አያስቆመውም ነበር? ” “ክፉ-ልብ ያለው ጨካኝ ነው፡” በማለት ተናግሯል፡ ጃይን፡ ወይም ጃክ ኮይን፡ ያወገዘ ጃይ ሉዊስ። አያችሁ። እንዲህ አለ፦ “ክፉ-ልብ ያለው ጨካኝ ነው። እንዲህ ብሎ አምላክ የለም። እንዲህ′ማ ከሆነ፡ እንዲህ እና እንዲያ... ” ኦህ፡ እንደው... ያልተሳደበው የስድብ አይነት የለም፡ አያችሁ። ይህ ግን ምናልባት **እዚህ** ብዙ እውቀት ስላካበተ፡ **በዚያኛው** ግን ባዶ ስለሆነ ብቻ ነው።

43 አያችሁ፡ እሱ የደረሰው፡ እዚህ ነው። አያችሁ? ቃል ይናገራል፡ እሱም ሰውሮታል። አስታውሱ፡ ምስጢሮች ሁሉ አሁን የተሰወሩ ናቸው፡ መጽሀፍ ሲናገር፡ “ከዓለም ምስረታ ጀምሮ፡ የእግዚአብሔር ልጆች እስኪገለጡ ድረስ ይጠብቃል” ይላል፡ ይህም ለቤተ ክርስትያን ይገልጣቸው ዘንድ ነው። ኦህ፡ ማይ! ገብቷችኋል?

44 አሁን ለአፍታ ያህል ብቻ ነገሬ ቆም ላርገውና፡ ወይም ይህን እንድትረዱት... ወደ ቀጣይ ሐሳቤ እልፋለሁ። አሁን አስታውሱ፡ እንደ ቅዱስ ቃል መሰረት፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ እስኪገለጡ፡ በዘመናት ሁሉ ላይ፣ እስከ ሙሴ ዘመን ድረስ፣ እስከ ነብያት ሁሉ ዘመን ድረስ፣ እስከ አሁን የዘመን ፍጻሜ ድረስ ተጠባብቀዉታል። አዎን፡ ይህም ለእግዚአብሄር ልጆች ሊገለጥላቸው ስለሚገባ ነው። ለምን? እንደተናገርኩት፡ ከጥፋቱ... እስከ ፒራሚዱ፡ ወደ ግንባታው እየቀረበ፣ እየቀረበ፣ እየቀረበ ነበር።

45 ደጋግሜ እንደገለጽኩት፡ እና እንዳልኩት፡ ጌታ ሦስት መጽሐፍ ቅዱሶችን ሰርቷል። አንደኛው፡ ሰማይ ላይ ነው፡ ዞዲያክ ይባላል። ዞድያክን አይታችሁት ታውቃላችሁ? የዞድያክ ምስል በምን ይጀምራል? በድንግል። የመጨረሻው የዞድያክ ምስልስ? በአንበሳው በልዮ ነው። መጀመርያ ሲመጣ ወደ ድንግሊቱ መጣ፡ ዳግም ሲመጣ ግን የይሁዳ ነገድ አንበሳ ሆነ። አያችሁ?

46 ሁለተኛው በሄኖክ ዘመን ፒራሚዱን በሰሩ ጊዜ፡ በፒራሚድ ውስጥ ሠራው። ልኬቱን ለክተውታል። እኔ ራሴ አልገባኝም። ለጦርነቶቹ ግን፡ ለረጅም ጊዜ አቀርቅረው በጉልበታቸው በመሄድ፡ የጦርነቶችን ርቀቶች ለክተውታል። አሁን የቱ ጋር እንደሚለኩ ታውቃላችህ? በንጉሱ እልፍኝ አጠገብ። ፒራሚዱ በረዘመ ቁጥር... ዛሬ ባሉን መሳርያዎች ተጠቅመን፡ እኛ ልንገነባው አንችልም። ልንገናባው አንችልም።

47 ግንባታው **እንዲህ** አይነት፡ ወደ ላይ እየጠበበ የሚወጣ ነው። አናቱ ላይ ያለው ድንጋይ... የመደምደሚያ ድንጋይ እስከ አሁን አልተገኘም። በፒራሚዱ ራስ ላይ መደምደሚያ አላደረጉበትም። የምታውቁት ከሆነ እኔ እንጃ፡ የግብጽ ትልቁ ፒራሚድ ላይ፡ አናቱ ላይ የመደምደሚያ ድንጋይ ኖሮት አያውቅም።

ለምን? አያችሁ፡ የመአዝን ራስ፡ የመደምደሚያው ድንጋይ የሆነውን፡ ክርስቶስ፡ ስለተናቀ ነው።

48 አሁን ግን ከሉተራን ዘመን፣ እና ከባፕቲስት ዘመን፣ ከሜቶዲስት ዘመን፣ ከጴንጤቆስጤ ዘመን ወጥተን፡ የመደምደሚያው ድንጋይ እንዲያርፍብን እየተጠባበቅን እና እየናፈቅን፡ በቀጥታ ወደ መደምደሚያው ድንጋይ እያደግን ስንመጣ፡ ህንጻው አልቋል። "የመአዝን ራስ መጣሉን፡" ከቅዱስ ቃል አላነበባችሁምን? በርግጥ፡ ያ ሰለ ሰለሞን ቤተ መቅደስ እንደሚናገር እናውቃለን። "የተናቀው ድንጋይ ግን የመአዝን ራስ ሆኗል።" ይሄን የምልበት ብቸኛው ምክንያት በእናንተ ላይ አ—አ—አ—እንዲት ሰዕል ለመጫር ነው።

49 እኛ አሁን፡ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መሰረት፡ በፍጻሜው ዘመን፡ በፒራሚዱ መደምደሚያ፡ በዞዲያክ አቆጣጠር በተሰቀለው አሳ በካንሰር ዘመን፡ አንበሳው ሊዮ በሚገለጥበት ዘመን እየኖርን እንገኛለን። አያችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች በሚገለጡበት፡ የመደምደሚያው ድንጋይ ወቅት ላይ ነን። የት እንዳለን አያችሁ? በዘመኑ መጨረሻ ላይ ነን።

50 በዚህ ሳምንት እነ ክሩሼቭ የተናገሩትን፡ ከጋዜጣ ያነበባችሁ ሰንቶች ናችሁ? ኦህ፡ እነሱ ተዘጋጅቷል፤ እኛም። አሜን። ተዘጋጅተናል! አያችሁ፡ በጣም ጥሩ። ኦህ፡ እንዴት—እንዴት ያለ—መታደል፡ እንዴት ያለ ወቅት ነው! አሁን እየኖርንበት ያለውን ወቅት ክርስትያኖች ሁሉ ቢያውቁት ኖሮ! ማይ!

51 ምን ይመስላችኋል? ይሄን ያየ፡ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፡ በመጨረሻው ዘመን የሚነሡ የእግዚአብሔር ልጆች፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወሩ ምሥጢራቶችን፡ በዘመኑ ፍጻሜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሊገልጡ እና ማሳየት እንዲችሉ፡ በምጥ እየተጠባበቀ፡ በመጨረሻው ዘመን የት እንደሚገለጡ አይቶ ጽፏል።

52 ስለዚህ አሁን ትክክል መሆናችንን እና አለመሆናችንን ለማየት፡ እንዲሁም መገለጥን እንድናገኝ፡ እንደገና፡ "ወደ ዓለም ምስረታው" እንመለስ። እግዚአብሔርን "ባባ" ብዬ በመጥራቴ ራሴን የተለየ ቅዱስ ሰው እንደማላደርግ ተሰፋ አደርጋለሁ። ይሁን እንጂ እናንተም ይሄን ማወቅ እንዲቻላችሁ ባባ ማለት እፈልጋለሁ። ባባ! ባባ ግን ልጆች እንዲኖሩት ስለፈለገ፡ ምን አደረገ? "መላእክት ይሁኑ፡" አለ። በዙርያውም መላእክት ሰፈሩ። ኦህ፡ ልዩ ነው። እነርሱም አመለኩት፡ በዚህም መገለጫው፡ አምላክ ተባለ። አስታውሱ ኤል (ኤ-ል)፣ ኤላህ፣ ኤሎሂም፣ ከእርሱ በቀር ሌላ የሌለው፡ ብቻውን-የሚኖር፡ እንደነበረ፡ አትርሱ። ለመጀመርያ ጊዜ በዙርያው የሰፈሩ ግን መላእክት ናቸው። መላእክት ግን፡ ከማምለክ በቀር ሌላ መሆን የማይችሉ ነበሩ። ሊወድቁ የማይችሉ ነበሩ። እንዲሁም፡ አይታመሙም፡ የማይሞቱ ፍጥረታት ናቸው። ስለዚህ፡ የፈውሱን ሐይል ሊገልጥባቸው ሰላልቻለ፣ ማዳኑንም ሊገልጥባቸው አልቻለም። ያኔ፡ ከዛ በኋላ፡ እንዲህ ሆነ…

53 ከዛ በኋላ፡ "የሚዳሰስ እና የሚጨበጥ ፍጥረት እንሰራለን፡" አለ። ምድርንም ሰራት። ምድርን ከሰራ በኋላ፡ የምድር ፍጥረታቶችን በሙሉ አደረገ፡ በመጨረሻም ሰውን አደረገ። ከምድር የሚወጣ ነገር ሁሉ ከ—ከ ፖሊዋግ ወይም ጄሊፊሽ ጀምሮ፣ በውሃ ላይ ከሚንሳፈፍ ሥጋ ከለበሰው፣ ከዚያ ጀምሮ፡ እስከ… ከዚያ እስከ እንቁራሪት ድረስ፡ እንቁራሪትን፡ ከህያዋን ሁሉ

መካከል፡ የተናቀች ፍጥረት ይሏታል። ከህያዋን ሁሉ የከበረው ደግሞ ሰው ነው። ከእንቁራሪት ወጥሎ ወደ እንሽላሊት፡ ከእንሽላሊት በኋላ እየቀጠለ እና እየቀጠለ እና እየቀጠለ፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ "እፍፍ፡" ባለ ቁጥር፡ ህይወት ይወጣል፤ "እፍፍ፡" ሲል ሌላ ትልቅ ህይወት ይቀጥላል። ለመጀመርያ ጊዜ፡ የእግዚአብሔር ምሳሌን ይዞ የተገለጠው ፍጥረት፡ ሰው ነበር። የሰው አፈጣጠር በእግዚአብሔር አምሳል ነውና፡ ከሰው በላይ የሚሆን፡ ምንም የለም፡ በፍጹም አልበረም፡ በፍጹም አይኖርም፡ ከዚህ በፊት አልተፈጠረም ከቶ አይፈጠርም። አያችሁ?

54 ከዛ በኋላ ወንድ፡ መላእክትን ካደረገ ብኋላ፡ የመጀመርያው ወንድ ሲያበጀው፣ ወንዱን አበጀ፡ በአንድ አካል ውስጥ፦ "ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።" ወንድ እና ሴት በአንድነት ነበር፡ ሴታዊት እና ወንዳወንድ ነበር። አስታውሱ፡ በዘፍጥረት 1 ላይ፡ አዳምን አበጅቶ ስጋ ላይ ሲያለብሰው፡ ወንድ እና ሴት አደረገ፡ ዘፍጥረት 2 ላይ፡ ምድርን የሚያርሳት፡ ስጋ የለበሰ ሰው ገና አልነበረም። በአምሳሉ የተፈጠረ ሰው ቢኖርም እንኳ፡ መሳርያ ይዞ ምድርን የሚያርስ ግን ገና አልነበረም። "እግዚአብሔር ምንድነው... " [ጉባኤው፡ "መንፈስ ነው" አለ።—አርታዒ።] አዎን በትክክል። አያችሁ? የመጀመሪያውን ሰው ፈጠረ። "ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።" አሁን፡ የመጀመሪያውን ሰው ሲፈጥር...

55 አሁን፣ አስታውሱ፣ አስቀድሞ ይህ ሁሉ በአንድነት በሐሳቡ ውስጥ የነበረ ነው። እሁድ ማታ ላይ ተናግሬዋለሁ። ቃል—ማለት በንግግር የተተነተነ ሐሳብ ነው። እግዚአብሔር እንዴት አምላክ እንደሚሆን፣ እንዴት እንደሚመለክ፣ እንዴት ፈዋሽ እንደሚሆን፣ እንዴት አዳኝ እንደሚሆን አስቀድሞ አስቦበታል። ቃሉን በተናገረው ጊዜ ግን፡ ለዘላለም የጸና ሆነ። እግዚአብሔር ቃሉን ተናገረ ማለት ሆነ ማለት ነው! ኦህ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፡ ቃሉን በዚህ መልኩ አሁን መያዝ በቻሉ! በትክክል! እንደ ዘመን ቆጣሪዎች... ጊዜ አስቆጥሯል ቢሉም፡ ወይም የአርኪኦሎጂ እና ሌሎች ባለሞያዎች፡ ዓለም ሚልዮኖች እና ሚልዮኖች እና ሚልዮኖች ዘመናት አስቆጥራለች ቢሉ። ምናልባት ትሪሊዮን እና ትሪሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት ሊሆን ይችላል፡ እኔ አላውቅም። ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ እኔ አላውቀውም። እግዚአብሔር በጊዜ ውስጥ አይኖርም። ቃሉን ከተናገረው በኋላ አንድ ደቂቃ ሆነው አይባልም። እርሱ አምላክ ነው። በእርሱ ዘንድ ጊዜ የለም።

56 እስከ ትላንት ማታ ድረስ፡ ማለቴ እስከ ትላንትና ማለዳ፡ ይሄን ተረድቼው አላውቅም ነበር። ትላንትና፡ እና ነገ የሚባል ነገር የለውም፡ ሁሌም የአሁን፡ ዘለአለማዊ ነው። "እኔ ነኝ" የሚል ቃል አስተውላችሁት ታውቃላችሁ? "የነበርኩ፡" ወይም "የወደፊቱ፡" ሳይሆን፡ ዘለአለማዊ ነው፡ አያችሁ፡ "እኔ ነኝ፡" ዘወትር "እኔ ነኝ።"

57 አሁን ግን፡ ነገሮችን በጊዜ ስርዓት ውስጥ ማስቀመጥ ፈለገ። መገለጫዎቹ ይሄን ያፈሩ ዘንድ፡ የሚያመልኩት መሥራት ነበረበት። ከዚያ በኋላ ሰውን አበጀ። ቀጥሎም፡ በሰውየው ውስጥ፡ ብቸኝነትን ተመለከተ። ስለዚህ፡ አሁን፡ በክርስቶስ እና በቤተ ክርስትያን መካከል፡ የነበረውን ታላቁን ሐሳቡ ለማየት፡ እግዚአብሄር ሴቲቱን ሲሰራት፡ ከአዳም ከጎኑ አጥንት ወስዶ፡ የአዳም ሴታዊ መንፈስን፡ በጎን አጥንቱ በማስገባት፡ ሰራት እንጂ፡

የተለየ አፈር አምጥቶ አልሰራትም። ስለዚህ እንደ ሴት የሚያደርገው ወንድ ካያችሁ፡ የሆነ ችግር ስላለበት ነው። ወንዳ ወንድ ለመምሰል የምትፈልግ ሴት ካያችሁም፡ የሆነ ችግር አለባት። እያችሁ፡ የሆነ ችግር አለ። ሁለቱ፡ የተለያዩ መንፈሶች ናቸው። ሁለቱም ግን፡ በውህደት፡ አንድን ስጋ ይሆናሉ፡ “ሁለቱ አንድ ይሆናሉና።” ስለዚህ ወንድ እና ሴት አድርጎ ስራቸው፡ ሁለቱም፡ በፍጹም እያረጁም፣ ፈጽመው አይሞቱም፣ ፈጽመው አይሸብቱም ነበር። እንደ እኛ፡ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ይተኛሉ፡ ሐጥያት ምን እንደሆነ ግን አያውቁም።

58 እዚህ ላይ የእባቡ ዘር በሚል ርዕስ፡ ሌላ ትምህርት ስለማዘጋጅ ለዛሬ ይሄን አልፈዋለሁ። ደግሞም፡ ይሄን ርዕስ እንድዳስስ ጠይቀውኛል። ግን እስኪ የተለየ ነገር የሚያሳየን ካለ ሰው ከመጣ እያለሁ። ማወቅ የምፈልገው ያ ነው፡ እያችሁ።

59 እንግዲህ፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን፡ ኃጢአት ሲገባ፡ ምን ተፈጠረ?

60 ከአንድ ሚሊዮን፣ እና ከመቶ ሚሊዮን ማይሎች በላይ፣ ከፍታ ላይ፣ **ይሄን** የሚያክል ትልቅ ሰፍራ አለ፣ ይህም ፍጹሙ የአጋፔ ፍቅር ነው። **ወደዚህ** አንድ እርምጃ በሄዳችሁ ቁጥር፡ አንድ ኢንች ይጠባል። ምድር ምን ያህል ጥቂት ጊዜ እንደቀራት እናንተም ታውቃላችሁ። የቀረን የጥላዎች የጥላ ጥላ ነው። ያላችሁ ይህ ብቻ ነው፣ እኔም ያለኝ፡ የአጋፔ ፍቅር የጥላዎች የጥላ ጥላ ብቻ ነው።

61 በውስጣችሁ የሆነ ነገር አላችሁ፡ ከሀያ አመት በላይ የሆናችሁ ሴቶች ሁላችሁ፡ ከሀያ አመት በላይ የሆናችሁ ወንዶች ሁላችሁ፡ እንዲቆይላችሁ የምትመኙት አንድ ነገር አላችሁ። ማለት ከአሰራ አምስት እስከ ሀያ፡ ያሉ አምስት አመታት ብቻ። ከሀያ በኋላ መሞት ትጀምራላችሁ። ከአሰራ አምስት ጀምሮ፣ እስከዚያ ድረስ፡ ገና በጉርምስና ዕድሜ ላይ ናችሁ። ከዚያ እስከ ሃያ ድረስ ብስል ትሆናላችሁ። ከሃያ በኋላ፡ ኦህ፡ “አሁን ሙሉ ሰው ሆኛለሁ፡” ትላላችሁ። ትላላችሁ እንጂ፡ አይደላችሁም። ምንም ብታደርጉ፡ እየነደዳችሁ እና እየሞታችሁ ነው። እግዚአብሔር እስከዚያ እድሜ ድረስ አደረጋችሁ፡ ከዛ በኋላ ግን ትሞታላችሁ። ምን ይሆናል? መሞት ትጀምራላችሁ፡ ነገር ግን በውስጣችሁ “እንደገና አሥራ ሰምንት አመት መሆን እፈልጋለሁ፡” የሚል ነገር ይኖራችኋል።

62 አሁን አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ተወልዳችሁ፡ እስከ ዛሬ አሥራ ሰምንት ዓመት ብትሆኑ ኖሮ? ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ከነበሩት ሃሳቦች ጋር የቀረ፡ ውድ ቅርስ ትሆኑ ነበር! ገና መጻተኛ አባቶች ወደዚህች ምድር ከመጣታቸው በፊት፡ ያቺን አሳብ ብቻ የያዘች ሴት ከነበርሽ። እያችሁ፡ ችግር አለ። እንደው፡ አምስት መቶ አመታት አስቆጥረሽ አሮጊት ሆነች ብትኖሪ ይሻልሽ ነበር።

63 እንግዲህ፦ “ወንድም ብራንሃም፡ አሁን፡ ጥሩ ሰሜት ይሰማኛል። ኦህ፡ አሰራ—አሰራ—አሰር ሰምንት ነኝ፣ አሰራ ሰድሰት ነኝ፡ ደሰተኛ ነኝ፡” ትይኝ ይሆናል። አንድ ነገር ልንገርሽ፡ የኔ ማር። እናትሽ በዚህ ቤተክርሰቲያን ውሰጥ ከሌለች፡ በዚህ ደቂቃ ላይ በህይወት መኖሯ እና አለመኖሯ እንዴት ታውቂያለሽ? የወንድ ጓደኛሽ ወይም የሴት ጓደኛህ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንዳልተገደለች እንዴት ታውቃለህ? ነገ ጠዋት በቤትህ ውሰጥ አሰከሬን ሆነህ እንደማታድር እንዴት ታውቃለህ? ዛሬ ምሽት በህይወትህ ከቤተክርሰትያን እንደምትወጣ እንዴት ታውቃለህ? ምንም ዋሰትና የለም። ዋሰትና የለህም። አሥራ አምስት፣

አሥራ ሁለት፣ አሥራ ዘጠኝ፣ ሰባ አምስት፣ ዘጠና፣ ወይም... ሁሉም ዋሰትና የለውም። ምን ላይ እንደቆማችሁ አታውቁም። በዚህ ሁሉ ግን የአሰራ አምስት፣ የአሰራ ሰምንት አመት ወጣት መሆን ያምራችኋል። እንዴት እንዲህ ልትሆኑ ቻላችሁ?

64 አሁን፣ አሰራ ሰምንት ላይ ብትመለሱ እና ምንም ባታድጉ፣ ፈጽማችሁ ባትታመሙ ፈጽማችሁ... እንዳንተ ሰዎች አብረውህ ሊኖሩህ ይገባል፡ ምክንያቱ በእድሜ ትበልጣለህ፡ አየህ። ሌሎች ዕድሜ ሲጨምሩ፡ አንተ ግን ቅርስ ሆነው ትቀራለህና። አብረሃቸው ብታረጅ ግን ክፋኛ ታረጃለህ። ይሁን እንጂ ከዛ በላይ እንዳትቀጥል የምትጠራህ የሆነች ነገር አለች። ትንሿ አጋፔ ይህች ናት፡ ከዚህ ሁሉ በላይ... እንድትሆን የምታደርግህ ትንሿ ጥላ ይህች ናት።

65 አሁን፡ በቀደም ማታ ላይ፡ ማለቴ ጠዋት፡ ሰባት ሰዓት ላይ፡ መንፈሰ ቅዱስ፡ በቸርነቱና በጸጋው፡ ከዚህ ሥጋ፡ እንደወሰደኝ አምናለሁ፡ በትክክል አምናለሁ። ነው አይደለም፡ አልልም፡ ወደዚያች ምድር ገብቼ ሰዎችን አይቻለሁ፡ ሰዎቹም ሁሉ ወጣቶች ነበሩ። በህይወቴ ካየኋቸው በጣም ቆንጆ ሰዎች ይልቅ ቆንጆዎች አይቻለሁ። ሲናገረኝ የነበረውም፡- "አንዳንዶቹ ዘጠና ዓመታቸው የነበሩ ናቸው። በአገልግሎትህ የተቀየሩ ናቸው፡ 'ወንድሜ! ወንድሜ!" የሚሉህ ሰለዚህ ነው አለኝ።

66 ያንን አካል፡ ሰማያዊ አካል ነው፡ ሰንሞት ተረት ሆነን አንቀርም፡ አካል ይኖረናል። ሁላችንም ብንሞት፡ አቶሚክ ቦንብ፡ በዚህ ደቂቃ፡ ቢያፈነዳን፣ ከአምስት ደቂቃ በኋላ የእርሰ በእርሳችን እጅ እየተጨባበጥን በመተቃቀፍ፣ እልል እያልን እና እያሸበሸብን፣ አብረን ለእግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን! የሰ፡ ሰር። ወንድም እና እህት ሰፔንሰር፣ እዚህ ካሉት ቀደምት ጥንዶች መካከል፡ ግንባር ቀደምት፡ አንዱ አሰራ ሰምንት፣ ሀያ አመት ሆነው ይገኙ ነበር። ወንድም ኔቪል ገና ወጣት፣ እኔም ወጣት ልጅ እንሆን ነበር። ሁላችንም እንዲሁ እንሆን ነበር... ይህ እውነት ነው። "ድንኳን የሚሆን ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፡ ሌላ የሚጠብቀን አለ።"

67 ሕፃን ልጅ ከእናቱ ሲወጣ፡ እንደ ተፈጥሯዊ ልደት፡ የሚወራጭ እግር እና ሰውነት፡ ወዘተ ብቻ ነው። ወጣት እመቤቶች፡ ሰላገላለጼ ይቅርታ አድርጉልኝ። ይሁን እንጂ፡ ከወጣ በኋላ፡ ህይወት ያለው የሚወራጭ ጡንቻ ነው። ወደ ምድር ሲመጣ፡ መጀመርያ፡ ትንፋሽ ይይዛል፣ ወድያውኑ ወደ ጨቅላው የሚመጣ መንፈሳዊ ባህርይ ያለው አካል አለ። በራሱ ጊዜ፡ ትንሿን ጭንቅላቱን በናቱ ጡት ላይ ተክሎ መጥባት ይጀምራል። እሱ እንዲህ ካላረገ፡ ወተቱ በራሱ አይወርድም።

68 ጥጃ ሲወለድ፡ ወድያው በእግሮቹ ለመቆም ጉልበት እንደሚያገኝ... አይታችሁ ታውቃላችሁ? ወድያው ወደ እናቱ ቀርቦ፡ ጡት ለመጥባት ይሰካል። ይህን ማን ነገረው? ኡህ፡ አዋና!

69 ምክንያቱ፡ ምድራዊው አካል ወደ ምድር ለመምጣት በቀረበ ጊዜ፡ ሊቀበለው የተዘጋጀ መንፈሳዊ አካል አለው። ልክ ይህ ሲሆን... ኡህ፡ ሀሌሉያ! "ድንኳን የሚሆን ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፡ ወዲያ ማዶ የሚጠብቀን አለ።" ልክ ከዚህኛው እንደወጣን፡ ቀዝቃዛ ውሃ አምጡልኝ ወደ ማይለው፣ ውሃ ወደማይጠማው፡ ምግብ ወደ ማይበላው፡ ከምድር አፈር ወዳልሆነው፡

ወደዚያኛው አካል እንገባለን። ይህም ግን መዳሰስ የሚችል፡ ስሜት እና ፍቅር ያለው፡ በሌላው ሁሉ ፍጹም የሆነ እውነተኛ አካል ነው። ይህ አይነቱ አካል ማዶ ላይ እየጠበቀን ነው። የዚሁ አካል ክፍሉ ነው። ሶስት ናቸው።

70 የዘለአለማዊ ህይወት ጉዞ በመሰውያው ስር ትጀምረዋለህ። የዘለአለማዊነት ጅማሬ እዚህ ነው። ኦህ! የዘለአለም ህይወት እዚሁ ትጀምራለህ። ከዛ በኋላ፡ የእግዚአብሄር ልጅ ሆነህ ዳግም ትወለዳለህ። ከዛ በመቀጠል፡ ከሞት በኋላ... ሞት ስጋህን አሸንፎት የልብ ምትህ ሲቆም፡ የሟች መንኲራኲሮች ረጭ ሲሉ፡ ያኔ የጥላው ጥላ የነበረች ትንሿ ጥላ፣ በአንድ ሴኮንድ ውስጥ የጥላው ጥላ ትሆናለች፣ ከዚያ ቀጥሎ ያለው ጥላ ይሆናል፡ ቀጣዩ ጥቂት ወጨፎ ይሆናል፣ ቀጣዩ ወራጅ ውሃ ይሆናል፣ ቀጥሎ ወንዝ ይሆናል፣ ቀጣዩም ውቅያኖስ ይሆናል፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚያ ማዶ በምትወዷቸው ሰዎች ፊት ቆማችሁ፣ እርስ በርሳችሁ የምትተዋወቁ፣ እርስ በርሳችሁ የምትዋደዱ ሰዎች፣ የሰማያዊ አካልን ልብስ ለብሳችሁ፡ ወጣት ሴትና ወጣት ወንድ ትሆናላችሁ። በትክክል እውነት ነው። የጌታ ኢየሱስ መምጣት እየጠበቃችሁ እዚያው ትቆያላችሁ። አንድ ቀን ግን የከበረው የእርሱን አካል... አስታውሱ፡ ያ አካል ሰማያዊ አካል እንጂ የከበረ አካል አይደለም፣ ሰማያዊ አካል ነው። አንድ ቀን ግን ሰማያዊው አካል ገነትን ትቶ ከኢየሱስ ጋር ይሄዳል።

71 "ታውቁ ዘንድ እላችኋለሁ፡" ሁለተኛው ተሰሎንቄ፡ 5ኛው ምዕራፍ፡ ወይም አንደኛው ተሰሎንቄ፣ 5ኛው ምዕራፍ፡ ከሁለት አንዳቸው፡ "እላችኋለሁ፡ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፣ ወንድሞች ሆይ፡ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፡ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደ ሞተና በሶስተኛው ቀን እንደ ተነሣ ካመንን፡ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፡ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር፡ አንቀድማቸውም" (ልዩ ቃል) "ያንቀላፉቱን አንቀድምም። ምክንያቱ የእግዚአብሔርም መለከት ይነፋል፡ በክርስቶስ የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።" ሰማያዊ አካሎች ወርደው ምድራዊውን፡ ማለት የከበረውን አካል ይለብሳሉ። "ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፡ በድንገት፡ በቅጽበት አይን እንለወጣለን፡ ጌታን በአየር ለመቀበል፡ ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን።"

72 "በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር እንደገና እስክበላ ድረስ ከወይኑ ፍሬ አልጠጣም ወይም አልበላም፡" በሰርጉ እራት ላይ። በሦስት ዓመት ተኩል የክርስቶስ-ተቃዋሚ ንግሥናውን ሲያጠናቅቅ፡ ዓለም ሁሉ ይፈራርሳል፡ አይሁዶች ይጠራሉ፡ ዮሴፍም ለአሕዛብ፡ ማለቴ ለአይሁዶች እራሱን ይገልጻል። ዮሴፍ ለወንድሞቹ እራሱን በገለጸላቸው ጊዜ፡ ከአሕዛብ ወገን አንድም ሰው በአጠገቡ እንዳልነበረ፡ አስታውሱ። በላካቸው ጊዜ... ታሪኩን ታውቁታላችሁ። ዮሴፍ፡ በነገር ሁሉ፡ ፍጹም የክርስቶስ ጥላ ነበር። ዮሴፍ ወንድሞቹን ከላካቸው በኋላ፡ ተመለሰው ወደ እርሱ ቀረቡና፡ አያቸው እርሱም ቢንያምን፣ እና ሌሎቹን ሁሉ አያቸው... እነርሱም፦ "ሰውዬው፡ ምን ሆነ! ወ—ወንድማችንን ዮሴፍን፡ ባልገደልነው አሉ።" አሁንም ክርስቶስ፡ እራሱን ሲገልጥላቸው፡ አይሁድ ስሕተት መፈጸማቸው ይረዳሉ። ዮሴፍም አልቻለም፡ ለማልቀስ፡ ትንሽ ቀረው፡ ስለዚህም ሚስቱንና ልጆቹን፡ ጠባቂዎቹ እና ሌሎቹ ሁሉ አስወጥቶ፡ ወደ ቤተ መንግስቱ አስገባቸው። አዎን በትክክል። ከዚህ ነገር በኋላ በአይሁድ

ፊት ብቻ፡ “እኔ ዮሴፍ ነኝ፡ ወንድማችሁ። ወንድማችሁ ነኝ፡” አላቸው። ያን ጊዜም በፊቱ ወድቀው መንቀጥቀጥ ጀመሩ፡ እንዲህም አሉ፦ “ወንድማችንን ገድለነዋልና፡ እንዳለቀልን አሁን አወቅን። ገድለነዋል ያልነው ወንድማችን፡ እነሆ ታላቅ ንጉሰ ሆነ።”

73 እርሱ ግን አላቸው፦ “እግዚአብሔር ሕይወትን ለማዳን በምክንያት አድርጓል።” እግዚአብሔር ይህን ያደረገው፡ እኛን አሕዛብን ለማዳን ነው። አሕዛብሰ በቤተ መንግሰት ውሰጥ ነበሩና። ሀሌ ሉያ! ዮሴፍ በገዛ ወንድሞቹ በመጣሉ ምክንያት፡ ሙሽራን አገኘ፤ ሙሽራይቱ ግን ከአሕዛብ ወገን ናት እንጂ፡ ከአይሁድ ወገን አይደለችም። በጣም ጥሩ።

74 አሁን፡ ወዴት እያመራን ነው? ይህን ክቡር ሥጋ ከለበሰን በኋላ፡ በሚመጣውም ታላቁ ዘመን፡ የከበረው አካል፡ ይህ ሰማያዊ አካል የከበረውን አካል ይለብሳል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አሁንሰ ገብቷቿል? እኔ ሄጄ “ወንድም ነቪል!” ብዬ እጠራዋለሁ፡ እሰኪ ትንሽ ምሳሌ ልሰጣችሁ። ወይም፦ “ወንድም ሂዩመሰ፡ ዛሬ ጠዋት ባባ ጋር ደርሰን እንምጣ።” አምላክ ነው። አዳኝ እና ፈዋሽ እንደሆነ፡ አሁን እውቀናል።

75 ኃጢአት የተባለ ፍጥረት አልነበረም። ይህ ተቀባይነት የለውም፡ አለው’ዴ? ኃጢአት ፍጥረት አይደለም። ኖ፡ ሰር! ፈጣሪ አንድ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ኃጢአት ግን መዛባት። ኃጢአት ማለት የተዛባ ጽድቅ ማለት ነው። ምንዝርና ምንድነው? የተዛባ ጽድቅ ነው። ውሸት ምንድነው? የተዛባ እውነት ነው። በትክክል። የመርገም ቃል ምንድነው? ከበረከት ይልቅ፡ የእግዚአብሔር በረከት እርግማን ቃል አድርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ ማምጣት ነው። ኃጢአት ፍጥረት አይደለም። ኃጢአት መዛባት ነው። ሰለዚህ ሰይጣን እግዚአብሔር የፈጠረውን ብቻ ያጣምማል እንጂ፡ ኃጢአትን መፍጠር አይችልም። ይህ በትክክል እውነት ነው። ሞት ማለት የተዛባ ሕይወት ነው።

76 አሁን፡ ይህን አሰተውሉ—ይህንን አሰተውሉ። ሰለዚህ ተጉዤ ሄጄ፡ እንዲህ እላቸዋለሁ፦ “ወንድም ሂዩምሰ፡ እኔ እና አንተ፡ ከወንድም ቢለር ጋር እና ከጥቂት ወንድሞች ጋር ሆነን፡ ወደ ባባ እግዚአብሄር እንውጣ። እና፡ እናንተም፡ ተራሮችን ትወዳላችሁ። ትንሽ ጉዞ እናድርግ እላቸዋለሁ... ”

“እዋን፡ እንወዳለን።”

77 “ኦህ፡ አዲሲቷ ምድር ማዶ ሁለት ሚልዮን ማይሎች ትርቃለች። ወደዚያ ሄደን፡ እንዝናና።”

78 “እኔ የማደርገው... ? ... ፀሀይ፡ ዘወትር ወደ ላይ ትወጣለች። ኢሳያሰ 66። እሰማችኋለሁ። እናንተ ትናገራላችሁ፡ እኔም እሰማችኋለሁ።” ልክ ነው።

79 እንደምታውቁት፡ እኔም ሁላችንም፡ ጉዞ ጀምረን እየተጓዝን ትንሽ ተጉዘን፡ አምሰት መቶ ወይም አንድ ሚልዮን አመታት ያክል ሄደን፡ እንኳዛለን፡ ምንም የተፈጠረ አየሰልም፡ አያችሁ። አሁን—ይህ አሁን ውሸት ይመሰላል፡ ነገር ግን እውነት ነው። አያችሁ፡ እውነት ነው፡ ምክንያቱ ዘለአለም እንጂ፡ በዚያ ጊዜ የለም። እና በዚያም ደርሼ፡ ዙርያውን አየሁት ሄድኩ፡ በዚያ—ማንን—እንዳገኘሁ ታውቃላችሁ? አልኩኝ፦ “እንዴ፡ እህት ጆርጂ ብሩሰ ናት! እህት ጆርጂ፡ ካየሁሽ፡ ብዙ ዘመናት አለፉ።” ቁርጥ እንደወትሮዋ ትመሰላለች። አያችሁ? አሰር ሚሊዮን አመት ሆኗታል፣ ግን ልክ እንደ ቀድሞዋ በወጣትነት

እድሜዋ ናት። የሆነ ሰው ጀርባውን ታሻሸዋለች፡ እኔም ምን እንደሆነ አየሁ፡ አቦ ሽማኔ ነው፡ አንበሳ።

እኔም "አቦ ሽማኔ፡ ዛሬ ማለዳህ እንዴት ነው? " አልኩት፤

80 እንደ ድመት "ሚያው፡" አለ። "ኦህ፣ እዚያ ወርጄ በዙሪያቸው ትልልቅ አበባዎች ካሉበት አንዳንድ እህቶች ጋር እያወራሁ፡ ዙሪያውን እየተመለከትን አምስት መቶ ዓመት ያህል ቆይተናል።" እንግዲህ፡ ይህም ውሸት ይመስላል፡ ግን እውነት ነው። ይህ ትክክል ነው። እግዚአብሄርም ከመጀመርያው ያሰበው አሳብ ይህ ነበር።

81 በቃ፡ ልብሽ ይባረክ፡ እህት ጆርጂ። ጉዳት ፈጽሞ የለም፡ ፈጽሞ አይታሰብም። ምሽት ላይ ወደ ተራራው አናት ላይ በመውጣት፡ "ባባ እግዚአብሄር ሆይ፡ ያኔ ጠፍቼ ነበር። ያኔ በኃጥያት ጭቃ ውስጥ ተዘፍቄ ነበር፡ ባባ እግዚአብሄር ሆይ፡ አንተ ግን አድነኸኛል፡" እንለዋለን።

82 ይሄን ፍቅር ለመግለጽ የሞከሩ አንዳንድ ሰዎች'ኮ፡ አብደዋል። ለምሳሌ፡ **የእግዚአብሔር ፍቅር** የሚል መዝሙር የመጨረሻዋ መሰመር፡ በአይምሮ በሽተኞች ተቋም ግድግዳ ላይ የፃፈ ሰው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጽ የሞከረ ሰው አብዷል። አንተን እና እኔ ለማዳን የወረደው ፍቅሩ፡ ኃጢአተኞችን ለማዳን እንዴት እንደኅበጠ፣ እንዴት እንዳደረገ። ስለ አምልኮ ብትሉ፡ መላእክት ስለ አምልኮ ምንም አያውቁም! መልአክ የሚያውቀው፡ ብቸኛው አምልኮ… ቆሞ ክንፎቹን ወደፊት ወደኋላ፡ እና ዙርያው ላይ እያወዛወዘ፡ "ሃሌሉያ! ሃሌሉያ!" ማለት ነው፡ አቤት ምሕረቱ! ስለ ማወቅ እማ ካላችሁ ጠፍቼ ነበር አሁን ግን ተገኘሁ፣ ሙት ነበርኩ፣ ህያው ሆኛለሁ! አምላኬ ሆይ፣ ኃጢአት ነበርኩ፣ ጭቃ ውስጥ ነበርኩ፣ በቆሻሻ መጣያ ተጥዬ ነበርኩ!

83 ከሕይወት የምታገኙት ምርጡ ነገር ይሄው ነው። የኮልጌት ቆሻሻ መጣያ አካባቢ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? እስካሁን ከማውቃቸው ቦታዎች ሁሉ በግማት አቻ የለውም። ያረጀው ጢስ ሲሸተኝ ያመኛል። በዚያ ሁሉ ጢስ ውስጥ ተጥለህ፡ ካስተር ኦይል ከጠጣህ በኋላ፡ ከውስጥ ወደ ውጭ እንደሚገለባበጥ፡ የሆድ ቁርጠት ተይዞሃል። አየህ፡ የመጨረሻ ታምመሃል! አይጦች ሊበሉህ ወዲያ ወዲህ ይርመሰመሳሉ። ሕይወት እንዲህ ናት። እጅግ አርጅተህ እራስህን መቆጣጠር ተስኖሃል። ድንገት ግን አንድ ሰው ሊያነሳህ እጁን ዘረጋ። ከወደቅክበት አንስቶ የአሰራ-ሰምንት-አመት ወጣት አድርጎ፡ በተራሮች ራስ ላይ አስቀመጠህ፣ ፍክት ወዳለው የጤና አበባ፡ ማይ፡ ወደ ጥሩ እና ንጹህ አየር፡ ወደ ጥሩና ቀዝቃዛ የሚጠጣ ውሃ። እንደገና ወደ ቆሻሻው መጣያ መመለስ ያምርሃልን? በጭራሽ፣ በጭራሽ፣ በጭራሽ፣ በጭራሽ ቆሻሻው መጣያ አያምርህም።

84 ወዳጆች ሆይ፡ ትርጉሙ፡ ይህ ነው። ራዕይ በሉት፡ ወይም ከሰውነት መውጣት በሉት፡ ምንም ይሁን፡ ራዕዩ ይሄው ነው። ነገሩ ያ ቢሆንም፡ የሚጎዱ ሰዎች ይኖራሉ ብዬ ስለምፈራ፣ ከሰውነት መውጣት ከምለው፡ ራዕይ ልበለው። አሁን፡ እግዚአብሔር… ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን ወደ እርሱ ለማምጣት እግዚአብሔር ምን አደረገ። እነዚህ ሰዎችስ፡ እነማን ናቸው? እንዴት ሆነላቸው… ምን ቢያደርጉ ነው ለዚህ በረከት የታሰቡት? እንዴት ተወጡት? እግዚአብሔር፡ በመጀመርያ፡ አንድ መልአክ ሳይፈጠር…

ማለቂያ የሌለው አምላክ መሆኑን ስንቶች ታውቃላችሁ? እንዲህ ካልሆነ፡ እግዚአብሔር አይደለም። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር፣ በማያልቀው ምህረቱ፣ ይህንን ከፈጠረ፡ ሉሲፈር እነዚህን ነገሮች እንደሚያደርግ አስቀድሞ አይቶት ነበር። ያንን መሰረት በማድረግ፡ ሁሉንም በነጻ የግል ውክልና ውስጥ አስገባቸው። አሁንም እናንተ በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ናችሁ፡ መልካምን እና ክፉ የሚያሳውቀው ዛፍ በእያንዳንዳችን ፊት ተቀምጧል፡ ምርጫው የአንተ ነው። ሉሲፈርም የተሳሳተውን መንገድ ከመረጡት ቀዳሚ እሱ ነው። እርሱን ለመምሰል ሞከረ፡ ሌላውን ሁሉ ለመግዛት፣ ሌሎችን በሙሉ ለማንበርከክ ሞከረ፡ ተሰገበገበ። የሁሉ ጅማሬ እዚህ ጋር ነው። አሁን፡ ይሄን ሰሙኝ። ኃጢአት የጀመረው በዚህ ነው። እግዚአብሄር፡ ማለቂያ በሌለው አሳቡ፡ ይሄን አየ፡ ብቸኛው አሰራሩንም አየ...

85 አሁን፣ እናንተ የሥላሴ እምነት ተከታይ ወንድሞች፣ እናንተን መጉዳት አልፈልግም፣ ነገር ግን በእግዚአብሄር መልካም ቃል ሰም ኢየሱስን ከራሱ ከእግዚአብሔር የተለየ አካል አድርጋችሁ ማሰቀመጥ እንዴት ትችላላችሁ? የምታዩትን ሰው ለማዳን፡ ኢየሱስ ሌላ አካል ተጠቅሞ፡ ሄዶ እንዲሞት ካስደረገው፡ ፍትሃዊነት የሌለው ፍጡር ነው። እግዚአብሔር ሊሰራበት የሚችልበት ብቸኛው መነገድ፡ እሱ ራሱ ቦታውን በመውሰድ ነው! እግዚአብሔርም የሞትን ሰቃይ ያይ ዘንድ፣ ሞትን እና መውጊያውን ከእኛ ያርቅ ዘንድ፣ በገዛ እጁ ይዋጀን ዘንድ ሥጋ ሆነ። ለዚህም ነው እርሱ እጅግ ይሚመለከው። በርግጥ ኢየሱስ ሰው ነበር፡ አዎን ነበር። ከድንግል ማርያም የተወለደ፡ ኤም-ኤ-ኤን፡ ሰው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በመንፈሱ ያለ ገደብ በእርሱ ውስጥ ነበር፡ በእርሱም የመለኮት ሙላት በሰውነት ተገልጦ ኖሯል። እሱ ያህዌ-ጅሬህ፣ ያህዌ-ራፋ፣ ያህዌ-ምናሴ፣ እራሱ ያህዌ፡ ጋሻችን፣ መከታችን፣ ፈውሳችን ነበር፣ እርሱ አልፋ፣ ኦሜጋ፣ መጀመሪያ እና መጨረሻ፣ እርሱ ፊተኛው፣ መጨረሻው ነበረ፣ የነበረ፣ ያለና፣ የሚመጣው እርሱ ነበር፣ የዳዊት ሥርና ዘር፣ የንጋት ኮከብ፣ እርሱ፡ ሁሉ-በሁሉ-ነው። በእርሱ የመለኮት ሙላት በአካል አደረ!

86 ሞትም ሰዎችን ሁሉ የሚነድፍበት፡ መውጊያ ነበረው፡ "እሃ፡" ይላል ዲያብሎስ፦ "እኔን ስለሰማኸኝ፡ አሁን አገኘሁህ። ወጋሁህ፣ መቃብር ውስጥ እከትሃለሁ። የበግ ደም ምንም ሊረዳህ አይችልም፡ ተራ የእንሰሳ ደም ነው ይል ነበር።" እግዚአብሔር ግን፡ በጥበቡ፡ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደው በግ፡ እንዲመጣ ያውቅ ነበር። አዎን፡ ጌታዬ። እነርሱንም... የዘመኑን ፍጻሜ እስኪመጣ ድረስ፡ ዘመኑን ጠበቀ።

87 አንድ ቀን ግን ይህ ሰው፡ ማለት በጉ በመጣ ጊዜ፣ ሰይጣንም ሳይቀር ተታሏል። ሰይጣን ዙሪያውን አይቶ፡ እንዲህ አለ፦ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፡ **ይህን** አድርግ። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ተአምር አድርግ እና ማድረግ መቻልህን አሳየኝ። ስታደርግ ልይህ። ኧሀ-ሃ፣ ፊቱ ላይ ጨርቅ አስርበታለሁ፣ መታሁህ። ነቢይ ከሆንክ፡ ማን እንደመታህ ንገረን።" አይይ! "አንተ እርሱ እንደሆንክ—አላምንም። ከሆንክ፡ እንዴት እንደሆንክ በቀጥታ ንገረን።" እየህ፡ በግልጽ። "ኦህ፡ እኔ ነኝ በል!" አፉን አልከፈተም። ኦህ፡ ኦህ፡ ያኔ አይኑን የሸፈነበት ጨርቅ ባነሳለት ጊዜ!

88 ዘወር ብሎ ወደ ደቀ መዝሙሩ አየና፡ “ብፈልግ፡ አሁን ከአባቴ ዘንድ ጠይቄ አስራ ሁለት ጭፍሮች መላእክቶችን እንዲልክልኝ ማድረግ እችል ነበር።” ታውቃላችሁ፡ ጲላጦስ ይህን አልሰማም።

89 “አንተ ከሆንክ! አንተ ከሆንክ። አይይ፣ እሱ አይደለም። ለምን፡ እዩት እየደማ ነው። ሄይ፡ እናንተ ወታደሮች ቀርባችሁ ፊቱ ላይ ትፉበት።” ተፉበት፣ ተሳለቁበት፣ እፍኝ ጢም ከፊቱ ነጩ። “አይይ፣ እሱ አይደለም! ኧረ፡ እሱ አይደለም! አሁን አገኘሁት። መውጊያዬን በደንብ እስካበታለሁ፡ እሺ። እስቅለዋለሁ!”

90 በመጨረሻም፡ “ኤሎሄ! ኤሎሄ! አምላኬ! አምላኬ!” “ለምን ተውኸኝ? ” ባለ ጊዜ ሰው ነበር።

91 በጌቴሴማኒ የአትክልት ስፍራ፣ ቅባቱ ተወው፣ አያችሁ፣ እንደ ኃጢአተኛ መሞት ነበረበት። እንደ ኃጢአተኛ ሆኖ ሞተ፡ ኃጥያቱ ግን የእኔና የእናንተ እንጂ፡ የሱ ኃጢአት አልነበረም። ያ ፍቅር የገባው እዛ ነው፡ የኔን እንዴት ወሰደ! ኡህ፡ ሃሌ ሉያ! የኔን እንዴት ወሰደ!

92 እነሆ እርሱ፡ በዚያ ሆኖ አፉን አልከፈተም። ወጊው እንዲህ አለ፦ “ታውቃላችሁ፡ ተራ ሰው እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። መውጊያዬን ስክቼበታለሁ፡ በድንግል የተወለደ አይደለም።”

93 መውጊያውን ስክቶበት ወጣ፡ ይሁን እንጂ ጊዜው ተቀየረ፡ ወዳጄ! የተሰካበትን መውጊያ ከራሱ ላይ ወድያውኑ ሰቦ አሰወጣ። ከዚያ ወዲህ መውጊያውን አንዴ ሰላወጣ፡ በድጋሚ መውጋት አይችልም። በሦስተኛ ቀን ከሙታን ተነሰቶ፡ እንዲህ አለ፦ “ሞቼም ነበርኩ፣ አሁንም ህያው ነኝ፣ ህያው ሆኜ ለዘለአለም እኖራለሁ፣ የሞት እና የሲኦል መክፈቻ አለኝ።” የሰ፡ ሰር። ሊያውቀው አልቻለም። “እኔ ህያው ነኝና፡ ህያዋን ትሆናላችሁ። አሁን ገና አልተገለጠም... ”

94 አንድ ቀን፣ ይህ ከሆነ ከሶሰት ከአራት ቀናት በኋላ፡ ወደ አብ ካረገ በኋላ፡ ተመልሶ መጣና፡ አንዳንዶች እንዲህ አሉ፦ “ኧረ፡ ይሄ ሰው... ምትሐት—ሳይሆን አይቀርም። ይህ ሰው ምትሐታዊ ነገር ሳይኖረው አይቀርም። እኛም... አይታችሁታል። እናንተም ራእዩን አይታችኋል አሉ።”

“ምትሐት አይደለም፡ እውነተኛ ኢየሱስ ነው።”

95 ቶማስም “እጆቹን እና እግሮቹን ዳሰሼ፡ ማን እንደሆነ እነግራችኋለሁ፡” አላቸው።

96 መጣና፦ “እነሆኝ፡” አላቸው። “አሳ ወይ እንጀራ አላችሁን? ሳንድዊች አምጡልኝ፡” አላቸው። ሳንድዊችም አመጡለትና በዚያ ቆሞ በላ። አላቸውም፦ “አሁን እኔ እንደበላሁ መንፈስ ይበላልን? መንፈስ እንደ እኔ ሥጋና አጥንት አለውን? ” አያችሁ? “እኔ እሱ ነኝ፡ እኔ ያ ነኝ።” አላቸው።

97 ጳውሎስም፦ “ምን ዓይነት አካል እንደሚኖረን ገና አልተገለጸም፣ እንደ እርሱ ያለ አካል እንደሚኖረን ግን እናውቃለን።” ምንድን? ቲዮፋኒ አካል ለብሶ ነበር’ዴ? የሰ፡ ሰር! ሲሞት፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ እንደገና በግል ተውላጠ ሰም “እሱ፡” “ወደ ሲኦል ሄዶ በእስር ላሉት ነፍሳት ሰብኳል” ይለናል። ሃሌ ሉያ! እንዴት አደረገው? የመዳሰሰ ስሜት ነበረው፣ የመሰማት ሰሜት ነበረው፣

የመናገር ክህሎት ነበረው፣ በቀደም ማታ እንዳየኋቸው የከበሩ ሰዎች ዓይነት ለብሶ ሰበከላቸው። በኖኅ ዘመን በነበረው ትዕግስቱ ንስሐ ያልገቡትን፡ በሲኦል ያሉትን ነፍሳት ወንጌል ሰበከላቸው።

98 በፋሲካ በተነሣ ጊዜ ግን፡ ያ አካል መበስበስን ያይ ዘንድ የማይቻል ሆኗል፣ ዳዊትም አስቀድሞ አይቶ፦ "ነፍሱን በሲኦል ውስጥ አልተዋትም፣ ቅዱሴን፡ መበስበስ ያይ ዘንድ አልተወውም። ነፍሴን በሲኦል አይተዋትምና፡ ሥጋዬም በተስፋ ያድራል፣ ቅዱሴንም መበስበስን ያይ ዘንድ አይተውም" ብሏል። ስለዚህ መበስበስ ከመጀመሩ ከሰባ-ሁለት ሰዓታት በፊት፡ በኖህ ዘመን በነበረው ትዕግስቱ ንስሐን ያልገቡን ሄዶ በእስር ላሉት ነፍሳት ወንጌልን የሰበከበት አካል፡ ያ ቲዮፈኒ፡ እንደገና ተነሳ፡ የሚሞተውም የማይሞተውን ለበሰ፡ ቆሞም በላ፡ ሰውም መሆኑን ነገረን። ሃሌ ሉያ!

99 ወንድም ኢቫንስ ሆይ፡ እሱን የምናየው በዚህ መልኩ ነው። በዳዊት ዙፋን የሚቀመጠውም ያኔ ነው። ሃሌ ሉያ! ያኔ ነው ተራራው እና ሸንተረሩ ላይ የምንመላለሰው፡ አብሬህ ለአንድ ሚሊዮን ዓመታት በተራሮች ላይ እጓዛለሁ፣ እየህ፣ ጥቂት ቀናት እዚህ፣ ጥቂት ደቂቃዎች በዚያ፣ እንሻገራለን፣ እዚያም እንቀመጣለን።

100 ምግብ ስንበላ፡ ታውቃላችሁ፡ ከሁሉ በፊት፡ እህት ዉድ የምትለው... እንዲህ እላታለሁ፦ "እህት ዉድ፡ ሆይ፡ ይህ ሁሉ ዘመን የት ነበርሽ? ይሄን ያህል ጊዜ አላየሁሽም... አስራ አምስት ደቂቃዎች ብቻ ያለፉ ይሰማኛል።"

"ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ከሁለት ሺ አመታት በፊት ነበር።"

101 "ኧረ-ሀህ። ምን እየተሰማሽ ነው?" ኦህ፡ ከደስታ በቀር ሌላ ምንም ስሜት የለም።

102 "ወንድሞቼ፡ ኑ ወደዚህ፡ ቅረቡ፡ ወንድሞቼ፡ ውድ ወንድሞቼ፡ የማሳያችሁ ነገር አለኝ። መቼም ጠጥታችሁት የማታውቁትን፡ የውኃ ምንጭ እዚህ አለ። ኧረ እንደውም፡ ቀዝቀዝ ያለ፡ ጥሩ ውኃ እንጠጣለን። እጄን ሰድጄ ትልቅ የወይን ዘለላ ቆርጬ አመጣለሁ፡ ሁላችንም ረፍቀን እንበላለን። ደስ አይልምን? በትክክል ደስ ይላል። ይሄው ነው።

103 ይህንን እንዴት አገኘነው? እንዴት አወቅነው? እግዚአብሔር፡ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ፡ ወሰኖናል! እነማንን? በተስፋይቱ ምድር ያሉትን።

> ... **በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ... በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች እንሆን ዘንድ** ወደ **ማደጎ አስቀድሞ ወሰነን፡**
>
> **እንዲያው** የጸጋው **ክብር ይመሰገን** ዘንድ...

እርሱ እንደተናገረው እናከብረው ዘንድ ነው። እግዚአብሄር እንዲሁ ነው። እንድናመሰግነው ዘንድ ያስፈልገናል።

> ... **የጸጋው ክብር ይመሰገን** ዘንድ፡ በውድ ልጁም **እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን ተቀበለን።** (በክርስቶስ ተቀብሎናል።)
>
> **በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን፡ እርሱም የሐጢአቶቻችን ስርየት** ኤስ-አይ-ኤን-ኤስ...

104 አሁን ወደ ማደጎ ልመለስና፡ ከዛ በፊት ግን ለጥቂት ደቂቃዎች “ኃጢአቶች” ላይ ጊዜ እወስዳለሁ። “ኃጢአቶች፡” ገብቷችኋል? እግዚአብሄር ኃጢአተኛን ኃጢአት ስለመስራቱ እንደማይፈርድበት ታውቃላችሁ? ኃጢአተኛ ስለሆነ ግን ይፈርድበታል። ኃጢአተኛ ሲጋራ በማጨሱ፡ አይፈርድበትም፡ ከመጀመርያም፡ ኃጢአተኛ ነው። አያችሁ? አያችሁ? ኃጢአተኛ፡ ኃጢአቶች የሉበትም። እንዲሁ ኃጢአተኛ ነው፡ እንጂ፡ ምንም ኃጢአቶች የሉበትም። እናንተ፡ ክርስቲያን የሆናችሁ ግን ኃጢአት አለባችሁ። አስተውሉ እዚህ ጋር የሚናገረው ቤተ ክርስቲያንን ነው። በመስመሯ ይጠብቃታል። አያችሁ? አያችሁ? “የኃጢአቶች ስርየት፡” ኤስ-አይ-ኤን-ኤስ። እኛ ሐጥያት እንፈጽማለን። ኃጢአተኛው ግን ኃጢአተኛ ነው፡ እግዚአብሄር አይሰርይለትም።

105 አሁን፡ እንዲህ “እሺ፡ ሄዶ ተኩሶ ሰው ገደለ። ይሄስ ምን ልትለው ነው? ” ትሉኛላችሁ፤ ያ የኔ ጉዳይ አይደለም። እኔ ሰባኪ ነኝ እንጂ፡ አራሚ አይደለሁም። ህጉ ውሳኔ ይሰጥበታል፡ አራሚዎች እነሱ ናቸውና። እነሱ… “እሺ፡” “እሱ’ኮ አመንዝረዋል፡” ትላላችሁ። ያ፡ ያ—ያ’ማ የህግ ጉዳይ ነው። ጉዳዩ በሱ እና በሕጉ መካከል ነው። እኔ—እኔ—እኔ—ግን አራሚ አይደለሁም፡ ሰዎችን አላርምም። እኔ እንዲለወጡ እሰራለሁ። አያችሁ፡ እኔ ሰባኪ ነኝ፡ ስራዬም ሰዎችን ወደ እግዚአብሄር ማምጣት ነው። ኃጢአት ከሠራ፣ ጉዳዩ ነው፣ ኃጢአተኛ ነው። እግዚአብሔር ከፍ ባለ ደረጃ ያወግዘዋል። ሲጀመር ኃጢአተኛ ነው፣ ከመጀመርያ ተፈርዶበታል። ወደ መጀመሪያው መሠረት እንኳን አይደርስም፣ እሱ—የትም—አይገኝም። ከመጀመርያ ጀምሮ ኃጢአተኛ ነው። ኃጢአተኛ ነው፡ ምንም ኃጢአቶች የሉበትም።

106 እንግዲህ “**ይሄን** ያህል ሌሊት ሆኗል፡ **ይሄን** ያህል ግን ሌሊት አይደለም፡” ማለት አትችልም። አይቻልም፡ ሌሊቱ፡ ሌሊት ነው። እግዚአብሔር እንዲሁ እንዲሆን ወስኖታል። አዎን፡ ኃጢአተኛውም ያው ነው፡ በቃ። “እንዲህ አርጓል፡ አሁንም፡ ሌሊቱ **ይህን** ያክል ነው፡ **ይህ** ሌሊት ብሩህ ሌሊት ነው።” አዎን አውቃለሁ፡ ነገር ግን፡ ሌሊት ነው። አያችሁ?

107 “በዚህ በኩል **ይሄን** ያክል ብርሃን ነው፡” ማለት አይቻለኝም። አልችልም፡ በቃ ብርሃን ብርሃን ነው፡ ብርሃንን፡ ይሄን ያክል በርቷል አይባልም። አያችሁ? **እዚች** ጋር ትንሽ ጥቁር ጠብታ ካለ ግን፡ ጨለማ መኖሩን መናገር ይቻላል።

108 ስለዚህ፡ “ኃጢአቶች” ኤስ-አይ-ኤን-ኤስ፡ የኃጢአቶቻችንን ስርየት (በምኑ? ) እናገኛለን፡ በውድ ደሙ።

**… እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን…**

109 እንዴት እንረሳዋለን? ኃጢአቶቻችንን ይቅር እንዲለን ያደረግነው ነገር አለን፡ ብቁ ስለሆንን ነውን? ምኑ አለ?

**… ጸጋው፡**

110 ኦህ፡ ማይ! ጌታ ሆይ፡ እጄ የሰራችልኝ ነገር የለኝም። ምንም ማድረግ አልችልም፡ ማድረግ የሚቻለኝ ነገር የለም። ተመልከት! አስቀድሞ ወሰነኝ፣ ጠራኝ፣ መረጠኝ። እኔ እሱን በፍጹም አልመረጥኩትም። መረጠኝ፣ መረጣችሁ፣ ሁላችንንም መረጠን። እኛ አልመረጥነውም። ኢየሱስም እንዲህ አለ፦ “እኔ መረጥኳችሁ እንጂ፡ እናንተ እኔን አልመረጣችሁኝም።” አለ፦ “አብ

ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፤ አብም የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። እና ከጥፋት ልጅ በስተቀር፡ አንዳቸውም አልጠፉም፡ እርሱም የተጻፈውን—ለመፈጸም ነው።” አያችሁ? አለ፦ “ነገር ግን አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።”

111 ኦህ፡ በጣም አርፍጃለሁ፡ አይደል? ገናም ከዚህ አልወጣሁም። በዚህ ላይ ዋናውን አልጀመርኩትም። ልፍጠን፣ በፍጥነት ወደ አንድ ነገር መድረስ አለብኝ፣ እና እንቸኩል። በአንድ ደቂቃ ውስጥ ወደ ማደጎ መመለስ አለብኝ። ይቅርታ አርጉልኝ፡ ለጥቂት—ደቂቃ ብቻ? ቶሎ ወደዚህ እንግባ፡ በጉባኤው ካሉ አንዳንድ ሰዎች ለዚህ ጉባኤ ብቻ ብለው ከጆርጂያ ድረስ የመጡ ናቸው፡ ጌታ ይባርካቸው። ስለዚህ፡ ከጆርጂያ፣ እና ከቴክሳስ ወይም ከሌላ የመጣችሁ ወንድሞች፡ 5ተኛው ቁጥር የሚናገረውን አድምጡኝ። ጥቂት ደቂቃዎችን እንውሰድና እንየው።

ወደ—ወደ አስቀድሞ ወሰነን...

112 “ወደ” የሚለውን ቃል ምን ያስረዳል፡ “ወደ” ማለት ምን ያሳያል? ወደ አንድ ነገር እየመጣን እንደሆነ፡ ያስረዳል። “ወደ ምንጩ እሄዳለሁ። ወደ ወንበሩ እየሄድኩ ነው።” ግገብቶሃል፡ ሂዩመስ? “ወደ ጠረጴዛው እየሄድኩ ነው።”

አሁን፣ **በኢየሱስ ክርስቶስ ለራሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰኖናል፡ በበጎ ፈቃዱ** በገዛ ራሱ **እንደ ወደደ፡**

113 በምን ያህል መውደድ? በማን መውደድ፡ በማን መልካምነት? በገዛ ራሱ። በበጎ ፈቃዱ በገዛ ራሱ እንደ ወደደ።

114 አሁን፡ “ማደጎ” ምንድነው? እስኪ ላብራራው... ምናልባት ይሄን ለማብራራት፡ ጊዜ ላይበቃኝ ይችላል፡ ይሁን እንጂ አነጣጥሬ እዳስሰዋለሁ። ከዚያ በኋላ ጥያቄ ካላችሁ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ምናልባት በመልእክት፡ ወይም በሌላ መንገድ ትጠይቁኛላችሁ። አድምጡኝ። ማደጎአችሁ መወለዳችሁ አይደለም። ማደጎአችሁ ርስትን መውረሳችሁ ነው። ዳግም ስትወለዱ፡ በዮሃንስ 1:17፡ ይመስለኛል፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ስንወለድ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ነን። ይሁን እንጂ አስቀድመን የተወሰንን ነበርን። የመጨረሻ ዘመን ልጆች ሆይ፡ እንድታዩት የፈለግኳችሁ ነገር ይህ ነው፡ አያችሁ፡ ምን... ልታዩ? (ወደ) ማደጎ አስቀድመን እንደተወሰንን።

115 እንግዲህ፡ ይሄውላችሁ። አሁን፡ ይሄ ነገር ጴጤቆስጤዎችን ያስቸግራቸዋል። እነሱ እንዲህ ይላሉ፦ “እኔ ዳግም ተወልጃለሁ! ጌታ ይባረክ፡ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ!” ይሁን። አዎን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። ትክክል ነው። ይሁን እንጂ አሁንም የተናገርኩት ይሄ አይደለም። አያችሁ፡ አስቀድሞ ወደ ማደጎ ተወሰናችሁ ነበር። ማደጎ፡ ለልጅህ ርስት ማውረስ ነው።

116 እጅግ ተጠግቼዋለሁ፡ ቤኪ እጅግ ተጠግተኸዋል እያለችኝ ናት፡ ከኋላ ያላችሁ ይሰማል። እኔ...

117 የብሉይ ኪዳን የማደጎ ህግ ስንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ? በትክክል፡ አይታችሁታል። አያችሁ፡ አንድ ልጅ። ወንድ ልጅ ሲወለድ። ከሰብከቶች በአንዱ ላይ ሰምቼዋለሁ። የትኛው ነበር፡ ስብከቱን ታስታውሰዋለሁ፡ ወንድም ጂን? ቴፕ ውስጥ ነው። ኦ፡ የትኛው ነበር? እ—እ—እ—አስታወስኩት። ኦህ፡ አሁን፡

እስታወስኩት፡ **እርሱን ሰሙት** ላይ ነው። የልጅነት ማደጎን፡ **እርሱን ሰሙት** ላይ አለ።

118 ስለዚህ፡ በብሉይ ኪዳን፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ—ህጻን ከተወለደ፡ ህጻኑ ከወላጆቹ ስለተወለደ፡ በተወለደ ጊዜ ልጅ ነው፡ የቤተሰቡ ወንድ ልጅ እና የሁሉ ወራሽ ይሆናል። የልጁ እድገት ግን በሞግዚቶች እጅ ስር ይሆናል። ገላትያ፡ ምዕራፍ 5፡ ከቁጥር 17 እስከ 25 ድረስ። በጣም ጥሩ። በሞግዚቶች፣ አሳዳጊዎች፣ አስተማሪዎች እጅ ስር ያድጋል። ማለት፡ ለምሳሌ፡ ወንድ ልጅ ከተወለደልኝ፡አባት፡ እባላለሁ...

119 ኪንግ ጀምስ ውስጥ ስታነቡት፡ ኪንግ ጀምስ ቨርዥን ውስጥ ያለው ሲነበብ በጣም እስቂኝ መሆኑን ስንቶች እሰባችሁ ታውቃላችሁ፣ እንዲህ ይላል፦ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖርያ አለ"? በቤት፡ ብዙ መኖርያዎች። አያችሁ? በትክክል፡ የኪንግ ጀምስ ዘመን—መጽሐፍ ቅዱስ በተተረጎመበት ወቅት፡ **ቤት** ማለት "ግዛት" ነው። "በአባቴ **ግዛት** ውስጥ ብዙ መኖርያዎች አሉ።" በቤት ውስጥ፡ መኖርያዎች ሳይሆን፡ የዚህን ግዛት አባት ተብሎ ይጠራ ነበር። መጽህፍ ቅዱሳዊ አድርገውት ነበር፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም እንዲሁ ነበር።

120 አንድ አባት እጅግ ብዙ ሄክታር እርሻ፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ሲኖረው፡ **በዚያ** ውስጥ፡ እጅግ ብዙ ሰዎች ይኖሩበት ነበር። በጎችን ሊጠብቁ የተቀጥሩ ቅጥረኞች **በዚያ** ይኖሩ ነበር፣ ከብቶችን የሚጠብቁም **በዚያ** ነበሩት፣ አንዳንዶቹ መቶ ማይል ርቀት ወዳለው ላይኛው ግዛት የሚወጡ **እዚህ** ጥቂቶች፣ ጥቂቶቹም ፍየሎችን የሚጠብቁ **እዚህ** ጋር፡ በቅሎዎችን እና-የተለያዩ ነገሮችን የሚጠብቁ ሌሎችም በዚያ ነበሩት። እጅግ ሰፊ—ግዛት ነበረው። አህያው ላይ ወጥቶ በየቦታው በመዞር እያንዳንዱ ሰው ምን እየሰራ እንዳለ ለማየት፣ የበግ-ሸለታው እና ሌላው ሁሉ ለማየት ወደ ሁሉም ይዞራል። ጊዜ አይበቃውም...

121 ከመድረኩ ከራቅኩኝ አይሰማችሁም። እዚሁ ለመቆም እ—እ—እሞክራለሁ። አሁንስ፡ በደንብ ይሰማችኋል? ተከታተሉኝ።

122 ግ—ግ—ግዛቱን—ለማስጠበቅ፡ ይጓዛል፡ ብዙ ይጋልባል። አሁን ግን... ይህ ወንድ ልጁ በንብረቱ ሁሉ ላይ ወራሽ ሊሆን ነው። ወራሽ ነው።

123 እኛም በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል፡ በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ስንወለድ፡ የሰማያዊው መንግስት ወራሾች ነን፡ እጣችንን እርሱ ተሸክሞልናልና፡ ከኢየሱስ ጋር አብረን-ወራሾች ነን። እኛ በእርሱ (ጽድቅ) እንሆን ዘንድ፡ እሱ የእኛን (ኃጢአት) ሆነ። አያችሁ? እኔ እሱ እሆን ዘንድ እሱ እኔን ሆነልኝ፡ አያችሁ፡ አብረነው-የምንወርስ ነን። በጣም ጥሩ፡ ሁላችሁ፡ ይህን አስታውሱ።

124 እግዚአብሄር፡ እናንተ ወደዚህ ደረጃ እንደምትበቁ፡ በቀደመው እውቀቱ፡ አስቀድሞ ወሰኗችኋል። የገባችሁ፡ እጃችሁን አንሡ፡ አያችሁ። እግዚአብሔር፡ በቀደመው እውቀቱ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንድትገቡ፡ አስቀድሞ ወሰናችሁ። ለዚህ ዘመን ክርስትያኖች የተሰፋ ምድር ምንድነው? ካወቃችሁት እጃችሁን አንሡ። "የተሰፋ ቃል ለእናንተ ለልጆቻችሁ፣ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው። በመጨረሻው ቀንም ይሆናል፣ በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ፣ በወንዶች እና በሴቶች ልጆቻችሁ ላይ ከመንፈሴ እፈሳለሁ፣ ይላል እግዚአብሔር።" ኢሳያስ

28፡18፦ “ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ነው። መልካም የሆነውን አጥብቃችሁ ያዙ። በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል፤ እርሱም። ዕዕረፍት—ይህች ናት አላቸው፡ እንዲገቡባት የተናገርኳቸው ሰንበት ይህች ናት አላቸው። እነርሱ ግን፡ እጃቸውን አወናጭፈው ሄዱ፡ መስማትን፡ እምቢ አሉ፣ መስማት አልፈለጉም።” አያችሁ? በትክክል።

125 ምን ማለት ነው? ልክ እነዚያ ከከነዓን፣ ወይም ከግብፅ እስከ ምድረበዳው ድረስ፣ እንደወጡት ሰዎች፡ እና የምድሪቱን ወይን ለመቅመስ ደጅ ላይ ደርሰው፡ ቀርበው እንደነበሩ ህዝቦች ነው። ወንድሜ፡ እነሱ፡ እንደ ዕብራውያን 6፡ ወደ ኋላ እንድሳብ ይፈልጉኛል። እንዴት አድርጌ? እነሱ አሰመሳይ አማኞች ናቸው፡ ፈጽመው አይሻገሩም! መሻገር አይችሉም። ኢየሱስም አለ፦ “አባቶቻችን… ”

እንዲህ አሉ፦ “አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ።”

126 ኢየሱስም “እነሱ’ማ፡ ሁሉም፡ ሞቱ፡” አላቸው። ተለይተዋል ማለት ነው። እነሱ’ማ፡ ሁሉም፡ ሞቱ። ትክክል ነው። አላቸው፦ “እኔ ግን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረድኩ የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ከዚህ እንጀራ የሚበላ ሰው ቢኖር፡ ፈጽሞ አይሞትትም። አዎን። የሰ፡ ሰር፡ ይሄን የበላ የዘለአለም ህይወት ያገኛል፡ የኤደን ገነቱ የህወት ዛፍ እኔ ነኝ።”

127 አያችሁ፡ ሰዎቹ’ኮ፡ እጅግ ተቃርበው ነበር! አያችሁ፡ ዕብራውያን 6 ላይ ካያችሁ፡ ወደ ኋላ ለመመለስ ፈልጌ ሳይሆን፡ ዕብራውያን 6 ላይ ግን፡ “እነዚህ ሰዎች እንዴ ተካፋዮች የነበሩ፣ እጅግ የተጠጉ፣ ከሰማያዊ ስጦታ የቀመሱ ነበሩ።” በዙርያው ቁጭ ብለው፡ ፈውስ ሲከናወን አይተዋል፣ ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ሲነኩ፣ የሰው ህይወት ሲቀየር ያዩ ናቸው፣ ጣታቸውን መጠቆም አይችሉም። ኖ፡ ሰር። ኖ፡ ሰር። “የሚመጣው ዓለም ኃይልም ቀምሰዋል፣ የተቀደሱበትንም የቃል ኪዳኑን ደም አሰበው፣ የእግዚአብሔርን ልጅ—ለራሳቸው እንደገና መሰቀላቸውን በመረዳት፣ ዳግመኛም ለንስሐ ራሳቸውን ለማደስ ቢሞክሩ… ”

128 “እኔ በቅድስና የምታምን ቸርች አባል ነኝ።” ከቀጠለ መልካም ነው፡ ነገር ግን ርቀት አትሄዱም። አያችሁ? የሰ፡ ሰር። ምድረበዳው ቀድሷቸዋል። አዎን፡ በትክክል። በምድረበዳው—የናሱ እባብ—እና የናሱ መሰውያ፣ ቅድስና፣ እና የተለያዩ ነገሮች ነበሯቸው፣ ይሁን እንጂ እረፍትን ለማግኘት ፍልሰጤም ገቡ። እንዲህ አይልምን…

129 ዕብራውያን ምዕራፍ 4 ተመልከቱ፣ “ሌላ ዕረፍት” አይልምን? እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ፈጠረ ሰባተኛውም ቀን እረፍት አድርጎ ሰጣቸው። “ዛሬ በዳዊት፡” በሌላ ሰፍራ ሰለ ሌላ የዕረፍት ቀን ይናገራል። ከዚያም ሌላ ዕረፍት ሰጣቸው፡ “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፡ እኔ አሳርፋችኋለሁ።” ወደ እረፍቴ ግቡ! እግዚአብሔር በሰንበት ከሰራው እንዳረፈ ወደ ዕረፍቱ የገባን እኛ ከሥራችን አርፈናል። በእውነት ቀርቶልናል። የሰንበት ዕረፍታችሁ ይህ ነው። እውነተኛው እረፍትታችን በተሰፋይቱ ምድር አለ።

130 መንፈስ ቅዱስ ለህዝቡ የተገባ የተሰፋ ቃል ነው። እና አጫጭር ልብስ ለብሰው ጸጉራቸውን እንዲቆርጡ ሊፒስቲክ እንዲቀባቡ፣ ወንዶቹም ቁማር እንዲጫውቱ እና ቢራ እየጠጡ ቀልድ እየተናገሩ፣ እንደዛው እንዲቀጥሉ የሚፈቅዱላቸው፣ ራሳቸውን የቸርች አባል ነን የሚሉ ምሁር ሰባኪዎችስ ለምን ይፈልጋሉ? ለምን፡ እንዲህ አይነት ነገር ተቀብለው የመንፈስ ቅዱስን አመራር እምቢ ይላሉ! መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር የእግዚአብሔር ቃል ሁለትም-አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፡ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፣ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል። አዎን፡ የአእምሮ አሳብ ሳይቀር ይመረምራል!

131 ዓለምን እና የዓለምን ነገር ከወደድን፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ውስጥ የለም። "ብዙዎች ተጠርተዋል፡ ጥቂቶች ተመርጠዋል፡ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ መንገዱም ቀጭን ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው። በዚያ ቀን ብዙዎች ወደ እኔ ይመጣሉ በመንግሥትም ይቀመጣሉ፡" ኢየሱስ፦ "ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር ይቀመጣሉ። የመንግሥት ልጆች ግን ወደ ውጭ ይጣላሉ፡ 'ጌታ ሆይ፡ **ይህን** በስምህ አላደረግንምን? አልሰበክንምን? ዶክተር **እከሌ-እና-እከሌ** አልነበርንምን እና ሬቨረንድ **እከሌ-እና-እከሌ** አልነበርኩምን? ይላሉ' 'ከእኔ ራቁ። በፍጹም አላውቃችሁም፡ እናንተ አመጸኞች፡ እኔ አላውቃችሁም።' 'ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡' የሚል ሁሉ፡ የሚገባ አይደለም። ነገር ግን በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እርሱ ይገባል፡ ወደ ውስጥ የሚገባው እርሱ ነው።"

132 ይሄው፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር ግቡ። እንዴት እንገባለን? አስቀድመን ተወሰነናል። ቤተክርስቲያን፣ በእግዚአብሔር አስቀድሞ በማወቅ፣ አስቀድማ ተወሰናለች (ለምን?) ለእርሱ ክብር፡ በጸጋው፡ ለክብሩ፡ ለአምልኮው እና ለእግዚአብሄር ክብር ነው። ባባ፡ ያኔ በመጀመርያ፡ በዙርያው ማንም ሳይኖር፣ ብቻውን-የሚኖር ሳለ፣ አምልኮን ፈለገ፣ በዚህም ምክንያት ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አንዲት ቤተ ክርስትያንን አስቀድሞ ወሰነ፣ አስቀድሞ ሾማቸው፡ ስሞቻቸውም ዓለም ሳይፈጠር በታረደው፣ በበጉ የሕይወት መጽሀፍ ውስጥ... ጻፈላቸው፣ ሁሉንም በአንዱ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ በሚሰበሰብበት ጊዜ፣ በዘመኑ ፍጻሜ ለክብሩና ለምስጋናው፡ ይገለጡ ዘንድ ነው። ዋው! ክብር! ይሄው ነው። ሌላ የለም... ወንድም፡ እህቴ፡ እውነቱ ይሄው ነው። ከዚህ ፈጽማችሁ ፈቀቅ እንዳትሉ።

133 እግዚአብሔር እራሱ፡ በጸጋው አመራረጥ፡ ጠራችሁ። እግዚአብሔር እራሱ፡ በጸጋው አመራረጥ፡ ቀደሳችሁ። እግዚአብሔር እራሱ፡ በጸጋው እና በኃይሉ አመራረጥ፡ አጠመቃችሁ ወደ ዕረፍት ምድር አስገባችሁ። ወደዚህ ዕረፍት የገቡት ሁሉ ከክፉ ስራዎቻቸው አርፈዋል። እግዚአብሔር ከስራው እንዳረፈ እነርሱም ከስራዎቻቸው አረፉ። የማይነገር ደስታ፡ እና የሞላ ክብር አላቸው! የሕይወት ዛፍ በውስጣቸው እያበበ ነው። ትዕግሥት፣ ጨዋነት፣ በጎነት፣ የትዕግሥት እምነት፣ የዋህነት፣ እምነት፣ ገርነት፣ ወዘተረፈ ተሞልተዋል። ተስፋቸው በክርስቶስ ኢየሱስ መልሕቅ ስለያዘ የሕይወት ዛፍ በውስጣቸው እያበበ ነው፡ የመንፈስ ቅዱስን ምስክር አማኞችን ተከትሎ በምልክቶች እና በድንቆች ይመሰክርላቸዋል። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።" ሲሄዱም፣ ድውያንን ይፈውሳሉ፣ አጋንንትን ያወጣሉ፣ በልሳኖች ይናገራሉ፣

ራእይንም ያያሉ። እነኚህ... ከእግዚአብሔር ጋር ይሄዳሉ፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ይነጋገራሉ። የጸኑ ናቸው፡ ዲያብሎስ አይወዘውዛቸውም፡ እይታቸው ሁሉ... ? ... የኋላቸውን እየረሱ፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደሚገኘው ከፍ ወዳለው ጥሪ ምልክት ይዘረጋሉ። እነኚህ ናቸው። እነኚህ ናቸው። ቤተ ክርስትያን ማለት ይህ ነው።

134 ወደዚያ እንዴት ደረሱ? "ጌታ ሆይ፡ አንድ ቀን፡ ሲጋራ ማጨስ ጀመርኩ፡ እናም ወደቅኩኝ፡ እናም ሳሰበው፡ አንተ ታውቃለህ... " ማለት አትችልም፤ ኦህ፡ ኖ፡ ኖ፡ ኖ፡ ኖ።

135 አስቀድሞ በመወሰን! እርሱ ጠርቶናል፡ እኛም ስንከተለው፦ "አምላክ ሆይ፣ የጠፉ እና ኃጢአተኞች ነበርን። ራሳችንን የምናድንበት አእምሮ አልነበረንም። የእርያ ባህርይ ነበረብን፣ ስንጀምር እርያዎች ነበርን" ማለት እንችላለን።

136 ወደ እሪያ ቤት ሄደህ አሮጊቷን አሳማ ጠርተህ፡ እንዲህ በላት፦ "አሁን፡ አንቺ አሮጊት፡ ስሚኝ፡ አንድ ነገር ልንገርሽ። የቦይ ፍሳሽ መጠጣትሽ ትክክል አይደለም ብትላት።"

137 "ኦይንቅ-ኦይንቅ፡" ብቻ ትልሃለች። አያችሁ? ይህ ማለት፡ እራስህን እንደማዳን ያህል ነው። በትክክል።

138 እንዲህ ብለህ፦ "እመቤት፡ እንዲህ አይነት ልብስ መልበስ ተገቢ አይደልም፡ በስርዓት መልበስ አለብሽ። **እንዲህ** ማድረግ አለብሽ። ወደዚህ ስፍራ አትሂጂ... የቁማር ፓርቲዎችን አትሳተፊ። ሲጋራ ማጨስ የለብሽም። **ይሄን** አታድርጊ። አንተም፡ **እነኚህን** ነገሮች ማድረግ የለብህም ብትሉት።"

139 "ኦይንቅ-ኦይንቅ፡ እኔ **የኦይንቅ-ኦይንቅ** አባል ነኝ፡" ይላችኋል። ኧረ-እንደው። "ኦይንቅ፡" ከዚህ በላይ ሌላ እውቀት የላቸውም። "በል በል እኔ ልንገርህ፡ የአንተን ያህል መልካምነት እኔም አለኝ። ኦይንቅ-ኦይንቅ!" በቃ፣ የመንፈስ ቅዱስን አመራር አይቀበሉም፣ መጽሐፍ ቅዱስም ዓለምን እና የዓለምን ነገር ብትወዱ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በእናንተ ውስጥ የለም ይላልና።

140 ልዩ ያደረጋቸው ምንድን ነው? ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ። ምን አገኛችሁ? ወደዚያች ምድር ገብታችኋል። ሌላ ምድር ላይ ደርሳችኋል። ወደዚያ እንዴት ደረሳችሁ? ምድሪቱም የተስፋ ምድር ናት። ምን አይነት ተስፋ? "በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፣ ይላል እግዚአብሔር፣ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ።" ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ ተስፋይቱ ምድር ተጠመቅን። አሜን። ወንድም እህቶቼ ሆይ፡ ሀሌ ሉያ፡ ቅንዓት በሌለበት፣ ጠላትነት በሌለበት፣ ምንም በሌለበት፣ በንጹህ ልብ! አንድ ወንድም ቢሳሳትም፣ ምንም ነገር ቢያደርግም ግድ የለኝም፣ ሄዳችሁ ትፈልጉታላችሁ።

141 በቅርብ ጊዜ አንድ ወንድም ባክ እርጎ፡ ፍለጋውን ወጣሁ። አንድ ወጣት ወዳጄ መጣና፡ "ተወው ይሂድ፡ ይሄ አጉል ሰው ነው።" አለኝ።

142 እኔም፦ "ልቤ ከወንድሜ ጋር የማይሆንበት ደረጃ ላይ ከደረሰኩ፡ መሰውያው እግር ስር መውደቅያዬ ጊዜ አሁን ነው፡ ምክንያቱ ከጸጋው ወድቄአለሁና።" "እስትንፋሱ በሰውነቱ ውስጥ እስካለች ድረስ እከተለዋለሁ፡ ምናልባት የሆነ መስመር ላይ እይዘዋለሁ፡" አልኩት። የስ፡ ስር። ሄጄ አገኘሁት፡

ሃሌ ሉያ፡ መልሼ አመጣሁት። የሰ፡ ሰር። አሁን ወደ መንጋው በደህና ተመልሷል። የሰ፡ ሰር። በዓለም ስሕተት በትክክል በተወሰደ ነበር።

143 ቀደም ብሎ ፖሊሱ በጠራኝ ጊዜ፡ በዚያ ተቀምጣ የነበረች ምስኪን ሴት በጠየቅኳት ጊዜ፡ እንዲህ አለኝ፦ "ስለዚህ፡ ይህች ሴት በእስር ጃኬት መጠፍነግ አለባት።" "እእምሮዋ ስተዋል፡ ነውጠኛ ናት፡" አለኝ። እሷን—እሷን፡ ሆቴል ላይ አስቀመጧት። እና መጡ።

"ምንም ችግር የለውም።" አልኳቸው።

144 ፖሊሱም፡ እንዲህ አለ፦ "ለምን፡ ቢሊ!" ፖሊሱን በደንብ አውቀዋለሁ፡ ድሮ ህጻን ሳለው ጀምሬ አውቀዋለሁ። "ልረዳህ ማድረግ የምችለው ነገር ካለ፡" አለኝ።

"ምንም ችግር የለም፡" አልኩት።

"ልትረዳት ትችላለህ? " አለኝ፤

"አልችልም፡ **እርሱ** ግን ይችላል፡" አልኩት። "እስኪ አንድ ደቂቃ፡" አልኩት።

145 እና አመጧት። ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ በሰላም ወደ ቤቷ ሄደች። ያ ምን ነበር? ጸሎትን ጸለይንላት። አሜን! ከባድ ነገር ውስጥ ነበረች...

146 ባለቤትዋን ሲጠይቁት፦ "ዶክተር እንጥራላት? " "ዶክተር መጥራት ትፈልጋለህ? " አሉት፤

147 "ዶክተር ምንም አያደርግላትም፡" አላቸው። እውነቱን´ኮ ነው። እብድ ናት፡ ዶክተር ምንም አያደርግላትም።

"ብቸኛው ተስፋችን **እዚያ** መድረስ ብቻ ነው፡" አለው።

እሱም "ቢሊ፡ አልገባኝም፡" አለኝ።

እኔም፦ "እኔም ይገባሃል ብዬ አልጠብቅም፡" እየህ "እኔም አልጠበቅኩህም፡" አልኩት።

148 ግን´ኮ፡ ኦህ፡ እኔም፡ አልገባኝም! በጭራሽ። ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ እግዚአብሔር በሰማያት አለ... እኔም ያኔ ርቄ፡ ጠፍቼ ነበር፡ የሆነ ነገር ግን ተከተለኝ። አሜን! እኔ እንድመጣ ስለፈለግኩ አይደለም፡ በጭራሽ፡ ነገር ግን፡ የሆነ ነገር ተከትሎኛል። ምክንያቱም ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ሀሌ ሉያ፡ ለክብሩና ለምስጋናው እንሆን ዘንድ፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ወስኖናል። አድምጡኝ! አስቀድሞ ያወቃቸው፡ ምን አደረጋቸው? ጠራቸው። ልክ ነው? ጠርቷችኋልን? አዎን! ለምን ጠራችሁ? አስቀድሞ ስላወቃችሁ። አስቀድሞ ያወቃቸውን፣ ጠራቸው፣ የጠራቸውንም ደግሞ፡ አጸደቃቸው። ልክ ነው? ያጸደቃቸው፡ እነዚህን ደግሞ አከበራቸው! አሜን! መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል፦ "አስቀድሞ ያወቃቸውን፡ እነዚህን ደግሞ ጠራቸው።" በየትውልዱ! እርሱ የጠራቸው፡ እነዚያን ሁሉ አከበረ። ምንድን? ቅዱስ ቃል እዚህ ላይ ላንብብ። እሺ።

በበጎ ፈቃዱ **እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ፡ ለእርሱ ልጆች ልንሆን ወደ ማደጎ አስቀድሞ ወሰነን...**

የጸጋው **ክብር** ይመሰገን **ዘንድ...**

149 ኦህ፡ ገብቷችኋል? የጸጋው ክብር ይመስገን ዘንድ! በሚያሳልፋቸው በዘላለም ዘመናት ውስጥ በዚያ እንዲጸና፣ ልጆቹም ሁሉ “አባ፣ አባ! አባ፣ አባ!” የሚሉበት ድምጽ እንዲያጸና ነው፤

150 መላእክት ሁሉ በመገረም ይደነቃሉ፡ “ምን እያሉ ነው? ምን እየተናገሩ ነው?”

151 ይሄ ምሳሌ በጠፋው ልጅ ላይ በደንብ ተብራርቷል። “ጠፍቼ ነበረ።” “ልጄ ነው። ጠፍቶ ነበር አሁን ተገኝቷል። ሞቶ ነበር፣ እንደገና ሕያው ነው። የሰባውን ጥጃ፣ ምርጥ ልብስ፣ ቀለበት አምጡና በጣቱ ላይ አድርጉለት። ደስም ይበለን...” የንጋት ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ የእግዚአብሔር ልጆች የመዳንን እቅድ አይተው፡ በደስታ እልል ማለታቸው አያስደንቅምን፡ እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት ስማችሁን በመጽሐፍ ላይ አኑሮታልና።

152 “ካልቪንም እምነቱ እንዲህ አይነት ነገር ነበር፡” ልትሉኝ ትችላላችሁ። እኔ ካልቪንን አላምንም። ካልቪን’ኮ ነፍሰ ገዳይ ነበር። ካልቪን አንድ ሰው በኢየሱስ ስም ስለተጠመቀ ብቻ ለሞት ዳርጓል። እራሱ መለወጥ የሚያስፈልገው፡ ወፈፌ ነበር። አዎን፡ ወዳጄ። የተናገራቸው ነገሮች አንዳንዶቹ፡ ግን፡ ትክክል ነበሩ። የፈጸመው ነገር... የማይደረግ... ድርጊቱ ራሱ፡ በዚህ ምክንያት ሰውን የሚያጠፋ ሰው፡ አሰቃቂ ነው፡ ኃጢአት ነው። እሺ።

### ... ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን

153 ኦህ፡ ይቅርታ፡ “ማደጎን፡” አብራርቼ አልጨረስኩም አይደል? በጣም አርፍጃለሁ’ዴ? ምን ያህል ጊዜ እንደቀረን፡ ሰዓቱን እንየው። እሺ። ለ—ለነኚህ ከርቀት ለመጡ ሰዎች ሰንል አሰር ደቂቃዎችን እንውሰድ። ተከታተሉ። ተከታተሉኝ።

154 “ማደጎ፡” ለምን እንደሚደረግ አሳያችኋለሁ። ይህ አባት ትልቅ ግዛት አለው፡ በግዛቱም ይዞራል። እና ወንድ ልጅ ተወለደለት። ኦህ፡ በጣም ደስ አለው! (ይህ ማለት እግዚአብሔር ነው።) ሰውዬው ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ? ሰመ ጥር አሳዳጊ፣ ወይም ሞግዚት መፈለግ ይጀምራል። ሞግዚት ታውቃላችሁ፡ አይደል? የትምህርት ቤት መምህር ነው። በመላ አገሪቱ ሊያገኘው የሚችለውን በጣም ጥሩውን አስተማሪ ይፈልጋል። (አሁን እየቀጠልን ነን፡ አዳምጡ።) አለ የተባለውን ምርጥ የትምህርት ቤት መምህር ያገኛል። ልጁ ጀግና እንዲሆንለት ስለሚፈልግ፡ ተራ ወፈፌ ዘንድ አይወስደውም።

155 ልጆቻችሁን ጎበዝ እንዲሆኑላችሁ አትፈልጉም? በእርግጥ፡ ምርጡን ተሹላቸዋላችሁ! የሰ፡ ሰር። ታዲያ አንድ ፍጥረታዊ ሰው ይህን ካሰበ፣ እግዚአብሔር ለልጆቹ ምን ያሰብላቸዋል ትላላችሁ? አለ የተባለው ምርጡን ያሰባል።

156 ስለዚህ፡ ታማኝ ሰው ይፈልግለታል። አያችሁ፡ እንዲህ አይነት ሰው... አይፈልግም፡- “አሁን፡ ስማኝ፡ አ—አንተ ልጅ... መሆን ያማረህን፡ የፈለግከውን ሁን፡ እሺ፡” “ኦህ፡ አዎን፡ ጋሼ፡ አህ-ህህም በጣም ጎበዝ ልጅ ነው፡ እየለመደ ነው።” ባርኔጣው ላይ ገለባ ተከምሮበት ጀርባውን መታ መታ የሚያደርገው ሰው። ጭራሽ፡ አይፈልግም። እንዲህ አይነቱ ሰው ወድያውኑ ይባረራል።

በትክክል። እዉነተኛ የሆነ ሰው ይፈልጋል። ልጁ ትክክል ከሆነ፡ ትክክል ነህ ይለዋል። ካልሆነ፡ ስሕተቱን ይነግረዋል።

157 ስለዚህ ምድራዊ አባት ይህን ካሰበ... ሰውዬው ወይም የትምህርት ቤት አስተማሪው፡ ስለ ልጆቻችሁ ሐቀኛ እንዲሆን አትፈልጉምን? በትክክል። እሺ፡ እግዚአብሔርስ ምን የሚያስብ ይመስላችኋል? እርሱ ሁሉንም ያውቃል፡ እኛ አናውቅም፣ እሱ ያውቃል። እኛ ውሰንነት አለብን፡ ይሄ ነው ማለት አንችልም። እርሱ ግን ማለቂያ የለውም ያውቅበታል።

158 ስለዚህ፡ አብ ምን እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ? “ልጆቼን የሚያሳድግ ጳጳስ እቀጥራለሁ፡” በፍጹም አይልም። ወይም፡ “ቢሾፕ እ—እቀጥራለሁም፡” አላለም። በፍጹም፡ አላለም። ጳጳሱ፣ እንዲሁም ቢሾፑ እንደሚሳሳቱ ስለሚያውቅ፡ ያንን አያደርግም። አያችሁ? “አብያተ ክርስትያናቶቼን የሚቆጣጠር የበላይ ጠባቂ እሾማለሁ፡” በፍጹም አይልም። አይ፡ አይልም።

159 መንፈስ ቅዱስ አለለት። አህ-ህህ፡ ልጆቹን ለማሳደግ፡ ሞግዚቱ ይሄው ነው። እሺ። ታዲያ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያውቅ እንዴት ታውቃለህ? በሰው አንደበት ስለሚናገር። ታዲያ እሱ እውነት መናገሩን እንዴት ታውቃለህ? መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ እውነትን በሚናገር ከንፈር ትክክል ሲናገር ስታዩ፣ እንደ ሳሙኤል፡ የተናገራቸውን ትንቢቶች በትክክል ሲፈጸሙ፡ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ። አካሄዱ ትክክል ነው። እግዚአብሔርም፡- “አንድ ሰው ተናግሮ የተናገረው ነገር ካልተፈጸመ፡ አትስሙት፡ እኔ ከሱ ጋር አይደለሁምና አትስሙት። ከተፈጸመ ግን፡ እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ ያኔ፡ ስሙት።” አያችሁ? ይሄው ነው። አሰራሩም እንዲሁ ነው።

160 ከዛ በኋላ፡ ደርሼ ልምጣ ብሎ ይሄዳል። አሁን፡ ይህ ሞግዚት ወደ አብ ከሄደ ምን ብሎ የሚመሰክር ይመስላችኋል? እንዲህ ይላል፡- “የልጆችህ— የልጆችህ ስራ ክፉ ነው። ልንገርህ፡ በተለይ ይሄኛው ልጅህ፡ ይሄኛው፡ ኧረ፡ አመጸኛ ነው። ሞያ የለውም፡ እንዲህ አይነት ሰው ገጥሞኝ አያውቅም! እንዴ፡ ያደረገውን ልንገርህ? ይቺኛዋ ልጅህ ደግሞ! ኧረ፡ እንደው፡ ምን ልታደርጋት እንደሚሻልህ እንጃ። እህም። አየህ፡ ችግሯ ገብቶሃል? እንደው ነገረ ስራዋ ሁሉ... እዚያ ማዶ ላይ እንዳሉ ሴቶች። እንደ ፍልስጥኤማውያን መቀባባት ነው። አዎ፡ ጌታዬ፣ ልክ እነሱ እንደሚያደርጉት ማድረግ ትፈልጋለች።”

“ልጄ? ”

161 “አዎን፡ ሴት ልጅህ።” መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ስለ ቤተክርስቲያን የሚናገረው ይህንኑ ነው። ሪቫይቫል ሊኖረን ያልቻለበት ምክንያት ይህ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ያ እውነት ነው።

“ወንዱ ልጅህስ ቢሆን? ኧረ? እሱም ያው ነው።”

“ምንድን? ”

162 “ዘወትር የምትናገረው፡ አንተ ታውቀዋለህ በጎቹ ሁሉ የበጎች ምግብ ባለበት በዚያ ግጦሽ ራስ ላይ እንዲውሉ ዘወትር ትናገራለህ። ይሄኛው፡ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? ሁሉንም የአረም ክምር ወዳለበት ታች አወረዳቸው። ወደዚያ አወረዳቸውና ጅረት ውስጥ ጣላቸው፡ በዚያ የአረም ክምር ውስጥ እንዲወድቁ አደረጋቸው፡ አረግ እንዲበሉ አደረጋቸው፡ በጣም ስለከሱ ከዚያ

መውጣት አይችሉም።" እነዚህ ኃይሉን የሚክዱ ቢሾፖች፣ እና ፓስተሮች ናቸው። "በእውነት፡ እውነቱን ልንገርህ፡ በህይወቴ እንደነዚህ ቅብዝብዝ በጎች አይቼ አላውቅም።" እሱ ይሄን መሰማት አይፈልግም። በጭራሽ። "እና ምን እንደሆነ ታውቃለህ? እነኚያ ላሞችህ፡ አንተም እንዳዘዝካቸው—እንደምታውቀው፡ እንዲወፍሩልህ፡ ማዶ ላይ አልፋአልፋ—እንዲመገቡ አልነገርከውም?"

"አዎን።"

"ምን እንደሚሰጣቸው ታውቃለህ?"

"አላውቅም።"

163 "ከባድ እንክርዳዶች ያበላቸዋል። አዎን። ማሕበረሰብ እና ሌላ ነገሮች እንዲቀላቀሉ ያደርጋቸዋል። በህይወትህ እንደዚህ አይነት ነገር አይተህ አታውቁም። በሕይወት ዘመንህ እንዲህ ያለ ነገር አይተህ አታውቅም። ምን እየሰራ እንደሆነ ታውቃለህ? ወዲያ ወዲህ እያለ ትልቅ ሲጋራ እያጨሰ፡ ይኮፈሳል። ሚስቱም ከሱ ጋር ናት፡ ፍልስጤማውያን እንደሚያደርጉት ቁምጣ ለብሳለች። አዎ።" መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ስለ ቤተ ክርስቲያን የሚወስደው እንዲህ ዓይነት መልእክት ነው። አሁንስ፡ ስለዚህ ጉዳይ ምን ታስባላችሁ?

164 ማደጎ ማለት ይህ ነው። ምን... ምን አደረገን? አስቀድሞ—ወደ ማደጎ ወሰነን። መንፈስ ቅዱስን ሰጠን፡ ነገር ግን፣ አንድ ደቂቃ ቆይ፣ እየተነጋገርን ያለነው፡ ስለ ማደጎ ነው። ማደጎ!

165 "እና፡ ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? በቀደም ቢሾፑ መጣና፡ እንዲህ አለው። አንድ ሰው መጥቶ፡ አነስተኛ የፈውስ ጉባኤ እያካሄደ ነበር። እና ይህ ወጣት፡ ለበሽተኞች እየጸለየ፡ ቢሾፑ መጣና። ቢሾፑም 'አቁም እልሃለሁ!' አለው፤

"'ኦህ፡ ኦህ፡ እሺ፡ አባባ ቢሾፕ፡ እሺ አቆማለሁ።'

"'እንዲህ ዓይነቱ ነገር ላይ አትሳተፍ።'

"'ኦህ፡ አይ፡ አይ፡ አባባ ቢሾፕ፡ አልሳተፍም።'

166 "እና እኔም ጣልቃ ገባሁና እውነቱን ከቃልህ አሳየሁት። አየህ፡ ይሄ ነው አልኩት። ምን ማድረግ እንደሚገባው ከህጎችህ አውጥቼ አነበብኩለት፡ ይሁን እንጂ አልቀበልም አለኝ። እንዲህም አለ፦ 'ኦህ፡ ይሄ'ኮ የሌላ ዘመን ነው፡ ድሮ ለሌላ ልጅ የተመደበ። ያ ለእኔ አይደለም።'" ይሄውልህ። ይሄው ነው፡ ወዳጄ፡ ይህ እውነት ነው። አሁን ቤተክርስቲያን የት እንደጠፋች አይታያችሁምን፣ ለምን ሪቫይቫል እንደጠፋብን፣ ለምን ነገሮች አልሆን ማለታቸው ታያችሁን? ችግሩ ያለው እዚሁ ጋር ነው።

167 ኢያሱም እንዲህ አላቸው፦ "ጋድ፡ በንድፋ መሰረት... ርስትህ ከዚህ እስከዚህ ድረስ ተዘርግቶልሃል፡ ርስትህ እዚህ ጋር፡ ይኸው ነው። ጋድ ሆይ፡ ይኸው ውረስ፡ እና ኑርበት። ብንያም፡ ወደዚህ ውረድ። ሁላችሁ ከፍልስጤማውያን ድንበር ራቁ።" ኢያሱ ተመልሶ በመጣ ጊዜ፡ ሁሉም በፍልስጤማውያን መካከል፡ ትልቅ ባህላዊ ጭፈራ ላይ፡ እንዲህ ይወዛወዛሉ፣ ሴቶቹ ሁሉም ተቀባብተው፣ እየተወዛወዙ ልዩ ጊዜ እያሳለፉ አገኛቸው። ኢያሱም ጭንቅላቱን እከክ እከክ አረገና "አሁንስ ምን ይባላል?" አለ፤

አሁንም እየሆነ ያለው ነገር ይህ ነው፤ ሁሉም አይደሉም፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡ ሁሉም ባይሆኑም፡ እጅግ ብዙዎች። በጣም ጥሩ።

168 ያኔ የተፈጸመው ነገር? አሁን የሚሆነውም ያ ነው። ያ ሰው፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ፣ በአብ ፊት ይህ ነገር ሲናገር ፊቱ እንደሚቀላ አታስቡምን? ኦህ፡ ማይ! "እ—እ—እኔ'ኮ ነግሬዋለሁ፡ እ—እ—እሱ ግን አልሰማም አለኝ። ያንኑ ነግሬዋለሁ፡ እዚያ ከመጽሐፉ ውስጥ እንዲያነብ አድርጌዋለሁ። አንድ—አንድ ምስኪን አገልጋይ ወደኔ መጣና ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትናና ዛሬ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ አስተማርኩት። እና ምን እንደሆነ ታውቃለህ? እና ከድሮዎቹ የፍየል-መንጋ እረኞች መካከል—አንዱን አስመጣና ያ የሌላ ዘመን ነው ብሎ አስተማረው። አያችሁ? ታውቃለህ፣ እሱ በመጣ ጊዜ፡ ታውቃለህ፡ የፍየል፣ የሲጋራ፣ እጅግ መጥፎ ጠረን ነበረበት፣ እዚህ በደረሰ ጊዜ፡ በተለያዩ ነገሮች ምክንያት እጅግ ክፉ ጠረን ነበረው። አይገርምም? አንድ ነገር ግን ልንገርህ፡ የፍየሎች-እረኛው ጫንቃው ላይ እጅግ ብዙ ሜዳልያዎች፡ ያሉት ሰው ነው፡ እንደው፡ ስሙን በወረቀት ልጻፍ ብትል'ማ፡ (የግል ታሪኩ) የማዕርግ መጠርያዎቹን ለመዘርዘር ብቻ ግማሽ ሉክ ይፈጃል። አዎን፡ ጌታዬ፡ በምድር እጅግ የሚወደድ ነው፡ ነገር ግን፡ ልንገርህ፡ በጎችን እንዴት መመገብ እንዳለበት በፍጹም አያውቅም። አንዱ መጥፎ ነገሩ ይህ ነው። እኔን መስማት አይፈልግም፡" ይላል መንፈስ ቅዱስ። "ትላንትናና፡ ዛሬ እና ለዘላለም ያው እንደሆንክ፡ ልነግረው ሞከርኩ፣ እሱ ግን—ማመን አይፈልግም። በህይወቴ ካየኋቸው ቦቅቧቃ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ዋናው እሱ ነው። አዎን። ቤተ ክርስቲያንም የበላይ ጠባቂ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ወዘተ አድርጋዋለች፣ ስለዚህም ሕዝቡ ሁሉ እሱን እየሰሙት ነው። ሌላው ምን እንደሆነ ታውቃለህ? 'ቴሌቪዥን' የሚሏቸው... አንዳንድ ትንንሽ ነገሮች አሏቸው። እነዚያን ትንሽ ነገሮች **እንዲህ** ሰታበራቸው፡ እነኚያን ሴቶች—መጥተው የእርቃን ቀሚሶች ግማሽ ልብስ ለብሰው ሲውረገረጉ ይታያሉ። እናም፡ ታውቃለህ፡ ብዙዎቹ ሴቶች ልጆችህም አሉበት-... "

"ኦህ፡ እኔ አላምንም!" አያችሁ?

169 እሱም፦ "አዎን፡ እነሱም አሉ። አዎን፡ እነሱም ተካፋዮች ናቸው። አህም። አባ፡ አንዳንዶቹ ስለ ሪቫይቫል እያለቀሱ ናቸው፡ በጣም ከልባቸው ይፈልጉታል። አንዳንዶቹ መስመር ጠብቀው እየተጓዙ ይገኛሉ፡ አንዳንዶቹም በተቻለ መጠን ልክ እንደ ቃሉ ጸንተው ቆመዋል። ሌሎቹ ግን፡ እጅግ—እጅግ የራቁ ናቸው፡ ምን እንደማደርጋቸው አላውቅም። ሌሎቹ ምን እንደሚያደርጉ ታውቃለህ? እየተሳለቁባቸው፡ 'እነዚህ የፋራ ሰብሰብ፡'" ይሏቸዋል።

"በቃ፡ መጥፎ ስሜት እንዲሰማኝ አድርጎኛል።"

170 አህን ደግሞ ስዕሉን እንቀይረው። አሁን ያ አባት፡ ልጁ መልካም ነው። አባቱ ይሄው—ይሄው ነው፡ ሞግዚቱም፡ መንፈስ ቅዱስ ይሄው ነው። መንፈስ ቅዱስ፡ "በዚህ መንገድ እሄዳለሁ፡" ሲል፡ ሞግዚቱም ይላል፡ "እኔም... "

171 ማለት ልጁም "እኔም ከአንተ ጋር እጓዛለሁ። እኔም ከአንተው ጋር እሄዳለሁ፡" ይለዋል።

"ልጄ ሆይ፡ ሽለቆው፡ እጅግ ከፍ ያለ ነው።"

172 “እኔ አልለይህም አብሬህ እሄዳለሁ። በአንተ እተማመናለሁ። ቢደክመኝም፡ እጆቼን ከፍ ያደርጋቸውና ይደግፈኛል።”

“ግን’ኮ ሸለቆው ላይ አንበሶች አሉ!”

173 “ችግር የለም አንተ ከጎኔ እስካለህ ድረስ፡ ምንም ቢመጣ አልፈራም። ከአንተ ጋር አብሬህ እየተጓዝኩ ነው።”

“እዚያ ላይ ችግር አለ፡ አድካሚ ዓለቶች አሉ።”

174 “ምንም ይኑር፣ አንተ እጄን እስከያዝክ ድረስ፣ ከአንተ ጋር በትክክል እሄዳለሁ። አብሬህ በትክክል እሄዳለሁ።”

“ኦህ፡ ታውቃለህ? አባትህም ልክ እንዳንተ ነበር፣ አየህ። በጣም ጥሩ ነው። ይሄ፡ ነው።”

175 ኮረብታው አናት ላይ ደረሱ። እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡” “አብ፡ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ልጅህ ቁርጥ እንደ አባቱ ነው። ፍጹም፡ ልክ እንደ አንተ ነው። ለምትናገረው ቃል ሁሉ ‘አሜን’ ይላል። በቀደም—መጽሐፍ ቅዱስ ክፈት አልኩት፡ ‘ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡’ ይላል ቃሉ። ምን እንዳለ ታውቃለህ? እጆቹን ወደ ላይ አነሳና፡ በታላቅ ድምጽ ‘ሃሌ ሉያ! አሜን!’ አለ፤ ኦ! እና ቃሉ ምን እንደሚል ታውቀዋለህ፡ በ—በቃልህ ውስጥ፡ እንዲህ ብለህ የተናገርከው፡ ታውቀዋለህ፦ ‘እኔ የማደርገው ስራ፡ በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል? ”

176 “አዎን፣ ያንን ለልጄ እንደጻፍኩለት እስታውሳለሁ። አዎን፣ ያንን መፃፌ እስታውሳለሁ።”

177 “ኦህ፡ ያንን ሲያይ፡ ዝም ብሎ ጮኸና ወደ ላይ ወደ ታች እየዘለለ፡ ጮክ ብሎ፦ ‘ሃሌ ሉያ፡ ጌታ ሆይ። እንደዛ አድርገኝ። አለምን ሁሉ ከእኔ አስወግድልኝ!’ አዎን፡ ጌታዬ። ደግሞ ያደረጋቸው ነገሮች ብዛት!”

178 አባትዬውም፦ “ኦህ፡” “በልጄ—ኮራሁ። ጎበዝ ልጅ ነው። እንግዲህ። ጥቂት አመታት ተከታተለው፡ እንዴት—እንደሚሆን፡ እና እድገቱ እንዴት እንደሆነ ተከታተል።” ጥቂት አመታት አለፉ። “እንዴት እየሆነ ነው? ”

179 “ኦህ፡ ማይ፡ ኧረ በጸጋ እያደገነው! ኦህ፡ ማይ! እንደው... ጫካዎቹን እየመነጠራቸው ነው። እውነት እልሃለሁ፡ ል—ልጅህ ልዩ ነው... በጎቹን፡ ሲያስማራቸው፡ ልክ—ቁርጥ እንደ አንተ ነው። በፍጹም የባህር እንክርዳድ አያበላቸውም። በፍጹም ደረቅ እንክርዳድ አያበላቸውም። ‘ወደ ቤተ ክርስቲያን መቀላቀል እንፈልጋለን፡’ እያሉ ሲመጡበት፦ ‘ዝም በሉ፡ ይሄ አይጠቅማችሁም! ምንም፡ አይጠቅምም። ለእናንተ የሚያስፈልጋችሁ ይህ ነው፦ “ንስሓ ግቡ፡ ሐጥያታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ትቀበላላችሁ።”’ አዎን፡ ጌታዬ፡ የተናገረው ይህ ነው።”

“ኧረ፡ እውነት እንዲህ ብሏል? ”

“አዎን፡ ጌታዬ፡ በእርግጥ ብሏል።”

“እኔም’ኮ፡ የፃፍኩት በዚህ መንገድ ነው።”

“እርሱም የተናገረው እንዲሁ ነው።”

"እህም!" አዎን፡ ጌታዬ።

180 "አንዳንዶቹም፦ 'ከሰማይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ። መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ በኢየሩሳሌም፡ በይሁዳ እና በሰማርያ፡ እና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ሰለ'ኔ ትመሰክራላችሁ።' ይህን ቃል ባነበበው ጊዜ፡ 'ሃሌ ሉያ፡ የሚያስፈልጋችሁ ይህ ነው!' ብሎ ጮኸ፤ ምን እንደሚያደርግ ታውቃለህ? እስኪገባቸው ድረስ እዚያው ያቆያቸዋል፡ ያ ነው፡ እሱም በትክክል ከእነሱ ጋር ይቆያል።

181 "መረባበሽ ከጀመሩ ደግሞ፡ እንዲህ ይላቸዋል፦ 'ዋፕ፣ ዋፕ፣ ዋፕ፣ ቆይ አንድ ደቂቃ፡ አንድ ደቂቃ ጠብቁኝ። ፍየሎች እንጂ በጎች እንዲህ አያደርጉም' ይላቸዋል። አየህ? አየህ? ኦህ፣ አንዳንድ ጊዜ በጥቂቱ ይናደዱበታል፣ ነገር ግን በደግነት ጀርባቸው ላይ በሰሱ መታ መታ አርጎ፣ 'ሽ-ሽ፣ ሽ-ሽ፣ ሽ። አንድ ደቂቃ ጠብቁኝ፡' ይላቸዋል። አዎን፡ ጌታዬ፡ በእውነት እልሃለሁ። በጎችን እንዴት እንደሚቆጣጠራቸው በእውነት ያውቃል።

182 "ታውቃለህ? ቢሾፕ **እከሌ-እና-እከሌ** '**ወደዚህ** ከተማ መጥተህ ጉባኤ ማዘጋጀት አትችልም' ሲሉት ሰምቻቸዋለሁ። እንደምታውቀው ግን፡ ምሪት ሰጠሁት፡ እና፡ 'ዝም ብለህ ሂድ፡' አልኩት። አየህ? 'እነዚህ የቴፕ ቅጂዎችን ክፈትላቸው፡ እና እንዳትለቃቸው።' ለማንኛውም ሄድን! ወደ ከተሞች ሄድን እንዲህም አላቸው፦ 'እኛ፡ ስፖንሰር አናደርግም-... '

183 "ታውቃለህ፣ ዲያብሎስ ወደዚያ ወረደና፣ 'እኔ እሱን ከዚህ ከተማው እንደማባርረው፡' እወራረዳለሁ አለ። እኔም 'አትችልም። እኔ ሂድሂድ ካልኩት፡ ይሄዳል። እኔም ይሄዳል ብዬ እወራረዳለሁ፡' አልኩት። 'ኖ፡ ኖ፡ ኖ፡ ኖ፡ ኖ፡ እኔ እነግረዋለሁ። ወደ ታች ወርጄ፡ "አሁን፡ ወኪሎቼ በሙሉ፡ ሁላችሁም አንድ ላይ ተሰብሰቡ። ጊዜ ያለፈበት ወግ አጥባቂነት፡ ጊዜ ያለፈበት መለኮታዊ ፈውስ ጊዜ ያለፈበት የመንፈስ ቅዱስ ቀልዳቀልድ አያስፈልጋችሁም። ድሮ ከሐዋርያት ጋር ጠፍቷል። ድሮም፡ እንደማይጠቅም ታውቃላችሁ።'" ያረጁ ደረቅ እንክርዳዶችን፡ እና መሰል ነገሮችን ሊሰጣቸው ሞከረ። እነሱ...

184 "ምን እንደሆነ ግን፡ አውቀሃል፡ ለማንኛውም ወደዚያ ወረደ። ወደዚያ ወደ ታች ሄዶ አልፋልፋን መጣል ጀምረ... እና ምን እንደሆነ ታውቃለህ፡ በጎች መብላት ጀመሩ፡ አሁን እጅግ እየወፈሩ ነው። አዎን፡ ጌታዬ። ፈውሶች እና ሰብሰባዎች እየተደረጉ ነው፣ እና ታውቃለህ፣ አሁንማ ብዙዎቹ ወጣቶች ማግልገል ጀምሯል። ለምን፡ እንደዚያ አልፋልፋ ያሉ ትልልቅ ድርቆሽ ማግኘታቸውን አዩ። ምን እንዳደረጉ ታውቃለህ? ወደየ ጎረቤቶች ቤት እየሮጡ፡ 'ይህን ቅመሱ! ይህን ቅመሱ! ይህን ቅመሱ!' ማለት እስኪችሉ ድረስ እጅግ ጣፈጣቸው፤ አየህ፣ እዚያ ያለው ድባብ ልክ እዚህ እንዳለ አይነት ነው። ይሄውልህ ይሄኛው። ይሄውልህ እየው፡ ይሄ ነው። 'ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ በኢየሱስ ሰም ተጠመቁ፡ እነሆ፡ መንፈስ ቅዱስን ታገኛላችሁ። የሚፈልገው ሁሉ፡ አምጡት፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለማየት ይምጣ።' አየህ? አሁንማ ድንቅ ጊዜ እያሳለፉ ነው።"

185 "ኦህ፣ ልጄ ነው! ይሄ የኔ ልጅ ነው። ታድያ፡ በደንብ የበሰለ ይመሰልሃል? "

186 "አዎን፡ በደንብ በሰለዋል፡" አለ መንፈስ ቅዱስ። "ፈተናዎችን ፈትኜዋለሁ። ኧረ፡ **በዚህም** ፈተንኩት፡ **በዚያም** ፈተንኩት። ታች አወረድኩት፡

አሳመምኩት፡ ወደ ታች ወረወርኩት። ረጋገጥኩት፡ ዲያብሎስ ባለ በሌለ አቅሙ እንዲያሽው ፈቀድኩለት፡ እንደገና ተነሳ። ያው እንደ ድሮው ሆኖ ተነሳ። አየህ፡ እንደገና መጣ። አሳመምኩት። **እንዲህ** አረግኩት። ሆስፒታል ውስጥ ጣልኩት። ወደዚህ አወጣሁት **እንዲህ** አድርጌ፣ **እንዲያ** አደረግኩ። ሚስቱን በሱ ላይ አስነሣሁበት፣ ጎረቤቶቹን በእሱ ላይ አስነሣኋቸው፣ ሁሉንም ነገር ገለባበጥኩበት። ትንሽ ለውጥ እንኳን አላሳየም። ‘ቢገድለኝም’ኳ፡ እምነዋለሁ፡’ አለ። ቤተሰቡን ገደልኩበት። **ይሄን** ወሰድኩ፣ **ይህን** አደረግሁት፣ **ይህን** ሁሉ አደረግሁ፣ **ይህን**፣ **ያንን**፣ **ሌላም** ሁሉ አደረግሁበት። አሁንም ጸንቶ ቆመ፡ ‘ቢገድለኝም’ኳ፡ አገለግለዋለሁ! እሱ የኔ ነው!’”

187 “ኦ! አሁን’ማ፣ ወደ አንድ ልዩ ቦታ ጠርተነው በማደጎ ልንጠቀልለው እንደሚገባ አምናለሁ።”

188 እንግዲህ፣ አንድ አባት፣ በብሉይ ኪዳን፣ ልጁ ዕድሜው እንደ ደረሰ ሲረዳ፣ ወደ ማደጎ ጊዜው ይደርሳል። ወደ! ህጻናት ሆነው ይወለዳሉ፡ ወድያውኑ፡ ልጅ ይባላሉ። ይሁን እንጂ እስኪበስሉ፡ እና ማንነታቸውን እስኪያሳዩ ድረስ፡ ከተራ ልጅነት የዘለለ ሌላ አይኖራቸውም። ከዛ በኋላ ግን፡ ይጠራዋል።

189 ቤተ ክርስትያን ሆይ፡ ይኸው እዚህ ደርሰናል። ዝግጁ ናችሁ? አሁን ትንሽ መሽቷል፣ ለአንድ ደቂቃ ብቻ፡ ሁላችሁም ጣታችሁን ነከሱ፣ ነፍሳችሁን ቆንጠጥ፣ እና ልባችሁን ደገፍ አርጉ። አያችሁ? አሁን ቤተ ክርስትያንን ርስቷን ልናስይዛት ነው። ቤተ ክርስትያን ወደዚያ ሁኔታ ስትደርስ፡ “ምናሴ፡ ርስትህ ይኼ ነው። ኤፍሬም፡ አንተም እዚህ ነህ፡” ይላቸዋል።

190 ከዛ በኋላ አባትዬው፡ ወደ አንድ ልዩ ሰፍራ ይወስደውና፡ **እንዲህ** አይነት ከፍ ያለ ሰፍራ ላይ ያሰቀምጠዋል፡ ድግስ ያዘጋጃል፡ ሰው ሁሉ ይመጣል። እንዲህ ብሎ ያውጃል፦ “ይህ ልጄ እንደሆነ ሰው ሁሉ ይወቅልኝ፡ ልጄን በማደጎ የራሴ አድርጌዋለሁ። ከዛሬ ቀን ጀምሮ፡ ሰሙ ይህ ነው… ሁላችሁ እወቁልኝ፡ ልዩ ካባ፡ ልዩ ልብስ አልብሼዋለሁ። ሰሙም ልክ እንደ ሰሜ በማንኛውም ቼክ ላይ እንደሚታወቅ የሱም ሰም ያው እንደሆነ እወቁ። ልጄ ነው፡ ምንም’ኳ ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ልጄ የነበረ ቢሆንም፡ አሁን ግን በማደጎ የቤተሰቤ አካል አድርጌዋለሁ። መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ ጊዜ ጀምሮ፣ ልጄ ነው። አሁን ግን እርሱን በሥልጣን ርስት ላይ አሰቀምጬዋለሁ። እርሱ ያባረረው ይባረራል፣ እርሱ የቀጠረው ይቀጠራል።

191 “እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ፣ ይህን ዛፍ፣ ይህን ተራራ፣ ‘ተነቀል’ ብትሉት፡ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፣ ነገር ግን የተናገራችሁን እንደሚፈጸም ብታምኑ፣ ይሁን ያላችሁት ነገር ታገኛላችሁ።” አያችሁ? ይሄው፡ ይሄው ነው። አያችሁ? “አሁን ልጄ ነው።” ሰለማደጎ ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያነቡ፡ ልጁ በማደጎ ርስት… የሚሰጠው… ልጁ የበቃ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ነው።

192 እግዚአብሔርም፡ ኢየሱስን በተራራ ላይ ባወጣው ጊዜ በልጁ ላይ ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ወደዚያ ወሰዶ፣ ሦስት የምድር ምስክሮች ናቸው። ኢየሱስ፣ ሙሴና ኤልያስ፣ እግዚአብሔርም ተራራው ላይ ነበሩ። ተራራው ላይ ቆሙ። እንደምታውቁት መጀመሪያ ሲያዩ፡ የተመለከቱት ነገር፡ ኢየሱስ በፊታቸው ሲከብር ነው። ልክ ነው? የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል

መሆኑን ስንቶች ታውቃላችሁ? ምን አደረገ? ሞት የማይነካው ዘለአለማዊ ካባ—አለበሰው። እንዲህ ይላል፦ "ልብሱም እንደ ፀሐይ አበራ።" ልክ ነው? ደመናም ጋረዳቸው። እነ ጴጥሮስና ዮሐንስም፡ በግምባራቸው ወደቁ። ቀና ብለው፡ ሙሴ እና ኤልያስ፡ ቆመው ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ሙሴ ለስምንት መቶ ዓመታት ምልክት በሌለበት መቃብር ተቀብሮ፡ በሞት ቆይቷል። ኤልያስም ከአምስት መቶ ዓመት በፊት በሠረገላ ወደ ሰማይ ተወሰዷል። ዋው! አሁን ግን ተራራው ላይ ነበሩ! ከእርሱ ጋርም ይነጋገሩ ነበር። አያችሁ፡ እነርሱን ሊያሳየው፡ ይህ ሁሉ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያይ፡ ኢየሱስን አወጣው፡ ሁሉንም ነገር አሳይቶታል። ከእርሱም ጋር ተነጋገሩ፡ ከእርሱም ጋር አወሩ።

193 ጴጥሮስም እንደገና ፊቱን አቅንቶ ባየ ጊዜ ያየው ክብር ከኢየሱስ ተወስዶ፡ ኢየሱስን ብቻውን አየው፡ ድምፅም ከደመናው መጣና፡ አላቸው፦ "የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት! የእሱ ስም አሁን የራሴ ስም ነው። እርሱን ስሙት!" የማደኅ፡ ወይም በርስታቸው የሰፈሩ ልጆች፡ ማለት፡ ይህ ነው።

194 አሁን፣ እግዚአብሔር የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያንን ከኤፌሶን መጽሐፍ ልትረዳው የፈለጋት ነገር ይህ ነው። አያችሁ? ገባችሁ—ገብቷችኋል? እየመሸ ስለሆነ፡ ልጆችም እንቅልፍ እንቅልፍ እያላቸው ነውና፡ እናጠቃልለው። አያችሁ፡ እስከ መጨረሻዋ ክፍል፡ እስከ ቁጥር 13 ድረስ—መቀጠል ፈልጌ ነበር፡ "በተሰፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፡" ይሁን እንጂ፡ አሁን አልችልም። እሁድ እንጨርሰዋለን፡ እሺ። ተመልከቱ። አሁን፣ እንዴት እና፣ ምን እንዳስገባን፣ እና እንዴት በዚህ እንደተጠበቅን።

195 አሁን ግን እንዴት "በርስታችሁ፡" ገባችሁ? የመንግስቱ የበኩር ልጆች በመሆን በመንፈስ ቅዱስ የተወለዳችሁ እናንተ ናችሁ። ስንቶች ታውቃላችሁ? በጣም ጥሩ። ቀጥላችሁስ፡ አስቀድማችሁ ወደ ምን ተወሰናችሁ? ወደ ማደኅ። ምን ማለት ነው? ርስታችሁን ወደ መውረስ አስቀድማችሁ ተወሰናችኋል።

196 ኦህ፣ እህት ስኮት፣ እዚህ ውስጥ የሆነ ቦታ ላይ ቁጭ ብላ እንዳለች አምናለሁ። ዛሬ ቤት መጥተሽ ነበር አይደል? አንድ አዲስ ትምህርት በአገሪቱ በተለያዩ ሰፍራዎች ላይ፡ እና በምድር ሁሉ እየተዘዋወረ እንደሆነ፡ ብዙ፡ ሰምቻለሁ፡ ይህም ኢየሱስ በዚህ ምድር እንዳለ፡ በአካልም እየተመላለሰ መጥቶ፡ **ይህን** አደረገ የሚል ወሬ ነው። ውሸት ነው! እዚህ ያለው መንፈስ ቅዱሱ ነው፡ እሱም ቤተ ክርትያኒቱን ቦታ ለማስያዝ፣ ሰርዓት ለማስያዝ፣ ይገቡባትም ዘንድ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማድረስ እየሰራ ነው... ይህም ጠላቶች ሁሉ እንዲወገዱ ነው።

197 ምናሴ ርስቱን መውረስ አይችልም። የፈውስ አገልግሎት ግማሹን በሚሆንበት ጊዜ መውረስ አንችልም... ወጥቼ... ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው ብዬ ስሰብክ፡ የሰላሴ አማኞች ወንድሞች—መጥተው "አይ፡ እሱ'ኮ ኦንሊ ጂሰስ ነው፡" ይላሉ። ግማሻቸው "መለኮታዊ ፈውስ'ኳ ጥሩ ነው፡" እንዲህ እና እንዲያ በሚሉበት ሁኔታ መለኮታዊ ፈውስ ማካሄድ አልችልም፡ ብዙዎችም በጌታ ተአምራት ይደሰታሉ እንዲህም ይላሉ፦ "ይሁን፣ ወንድም ብራንሃም ነቢይ እንደሆነ አምናለሁ፣ አንድ ነገር ብቻ ልንገርህ። መንፈስ ከሱ ጋር እስካለ ድረስ፡ የሰዎችን ልብ እስካነበበ ድረስ፡ የእግዚአብሔር ሰው ነው። ትምህርቱ ሁሉ ግን ጥቅም የለውም፡ የበሰበሰ ነው።" እንዲህ አይነቱ ተራ

ነገር የሰማ ማን ነው? የእግዚአብሔር ነው ወይም የእግዚአብሔር አይደለም። አዎን። አንድም ሁሉ የእግዚአብሔር ነው ወይም ፈጽሞ የእግዚአብሔር አይደለም። እንደዚያ ነው። ታዲያ እንዴት ትወርሳላችሁ? ምናሴዎች ርስታቸውን አልጠበቁም፣ ኤፍሬም ርስቱን አልጠበቀም፣ ጋድ ርስቱን አልጠበቀም፣ ቢንያም ርስቱን አልጠበቀም፡ ሁሉም ፍልስጥኤማውያንን ተከትለው ሄዱ፡ ሁሉም ተደባለቁ። ወደ ርስታችን እንዴት ነው የምንገባው? እኛ ሁላችን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተወልደናል። ልክ ነው? ምን ለመሆን ነው የተወልድነው? አስቀድሞ ለመወሰን... ከተወለድን በኋላ፡ ለማደጎ ማለት ልጆች ለመሆን አስቀድመን ተወሰንን፡ በክርስቶስ አካል ውስጥ መግባት። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ?

198 የክርስቶስ አካል ምንድን ነው? አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹ አስተማሪዎች፣ አንዳንዶቹ ወንጌላውያን፣ አንዳንዶቹ እረኞች ናቸው። ልክ ነው? ለዚህ ተጠርተናል። ሌሎች የልሳኖች ስጦታዎች፣ ልሳን መተርጎም፣ ጥበብ፣ እውቀት፣ ተአምራት፣ ተአምራት ማድረግ፣ እና ሌሎች የተለያዩ ስጦታዎች አሏቸው። እነዚህን ሁሉ ምን ያደርጉታል? በሰሱ ይለማመዱታል። እንዴት? እኔ እንጃ ብቻ እንዲሁ ይለቁታል። አንዱ ይነሳል፡ በልሳን ይናገራል፡ ሌላኛው በላዩ ይቀጥላል፡ "ብልር፣ ብልር፣ ብልር፣ ብልር፣ ብሊ፡" ይላል። አህ-ህህ። ሰባኪው ይሰብካል፡ መሠዊያ ላይ ጥሪ ያደርጋል፡ አንዱም ይነሳና፡ በልሳኖችም ይናገራል፡ "ሃሌ ሉያ! ክብር ለእግዚአብሔር!" ስሰባኪው— ቅባቱ ስላልቆመ፡ መልዕክቱን ለመቀጠል ቢሞክር፡ ከዚያም ሰዎቹ "ኋላ ቀር፡" ይሉታል። አያችሁ፡ ስላልተማሩ ነው።

199 መጽሐፍ ቅዱስ የነቢያት መንፈስ ለነብያት ይገዛል ይላል። እግዚአብሔር የግራ መጋባት አምላክ አይደለም። እኔ እዚህ ሰቆም ወይም ሌላ አገልጋይ እዚህ በእግዚአብሔር ቅባት ስር እዚህ ሲቆም፣ የቱንም ያህል በልሳን መናገር ብትፈልግ፡እግዚአብሔር መልዕክቱን እስኪጨርስ ድረስ፡ ዝም በል። በልሳኖች የምትናገሩ ከሆነ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መድገም ብቻ ሊሆን አይገባም፣ እግዚአብሔርም በከንቱ አትድገሙ ብሏልና። ነገር ግን በቀጥታ ለአንድ ሰው መልእክት ይሁን። በመለየት ጸጋ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው ነገሩን በሚነገረው ጊዜ፡ አንድም ቀን ቅዱሳት መጻህፍትን በመደጋገም አድርጎ የሚያውቅ ከሆነ፡ በዚህ ቀን ብላችሁ ጠቁሙኝ። የደረሰባቸው ችግር ወይም እነርሱ ያደረጉት ነገር ይነግራቸዋል፣ እንዲሁም ማድረግ ያለባቸው ነገር እና ሊሆን ያለ ነገር፣ ወይም እንዲሁ የመሳሰሉ ነገሮች ይነግራል። ልክ ነው?

200 ልሳን እና ልሳን መተርጎምም እንዲሁ ነው! በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በልሳኖች የሚናገር አንድ ቢኖር፡ ሌላውም የሚተረጉም ቢኖር፡ እንዲህ ይበል፤ ወንድም ኔቪል በልሳን ቢናገር፣ እና ይህ ወንድም እንዲህ ብሎ፡ ፍቺውን ቢሰጥ፡- "ይህ ሰው ትላንት ወደዚህ ወጥቶ ማድረግ የማይገባውን ነገር እንዳደረገ ንገረው። ዛሬ ሐኪሙ ካንሰር አለብህ ብሎታል። ሂድ እና ንስህ ገብተህ እራስህን አርም፡ ተመልሰህ ናና ከእግዚ አብሔር ጋር ታረቅ በለው።"

ሰውዬውም "በእውነት፡ ይህ እውነት ነው፡" ይላል። ያኔ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው።

201 በዚህ መንገድ ግን እንዴት እናደርገዋለን? አያችሁ? ዝም ብሎ ብቻ፡ "ብላምባ፣ ብልር፣ ብልር፣ ብልር።" ዝም ብሎ ድንገተኛ፡ ለማንኛውም፡ በዚህ

ፈጽሞ መውረስ የለም። አሁን ይሄ… አያችሁ፡ ኤፌሶናውያን፡ አልገባቸውም እንጂ… አያችሁ፡ ሞክረው ነበር። እንዴት እንዳልገባቸው አያችሁ? ለእርሱ ልጆች እንድንሆን አስቀድሞ ወሰኖናል! ያልኩት ነገር የገባችሁ ስንቶች ናችሁ? እጆቻችሁን አንሡ። ልጅነት! አዎን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ተወልደናል፣ መንፈስ ቅዱስ ተቀብለናል፣ እንዲሁም፦ "አባ፡ አባ! ሃሌሉያ! ክብር ለእግዚአብሄር!" እንላለን፡ አዎን፡ ልጆች ነን፡ ነገር ግን የትም መድረስ አንችልም። ፍልሰጤማዊውን መምታት አንችልም።

202 ቢሊ ግራሃምን ተመልከቱት። መሐመዳውያን፣ "ማረጋገጫው የት አለህ፡" ይሉታል።

203 ጃክ ኮይን ተመልከቱት እዚያው ቆሟል። በእግዚአብሔር መኖር የማያምን፣ የክርስቶስ ቤተክርስትያን በእግዚአብሔር መኖር ከማያምኑት ጋር እጇን ትጨባበጣለች፣ ትስማማለች። ክርስቲያን ነው ተብሎ የሚታሰብ፡ እንደ ጆ ሉዊስ ካለው ሰይጣን፡ እና የነጻ እሳቤ አመለካከት ያለው ሰው፣ እግዚአብሔር ከሚራገም እና "እንደውም፡ ሲጀመር፡ እግዚአብሔር ብሎ ነገር የለም፡" ወዘተረፈ፡ ብሎ ከሚናገር መጨባበጥ። ራሳቸውን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ቤተ ክርስቲያን፣ ወንድም ጃክ ኮይን በመቃወም፡ ከዚህ ሰው ጋር ይጨባበጣሉ። ሌላውስ ሁሉ እንዴት እናደርጋለን? የምድራችን አገልጋዮች በሙሉ፡ ጴንጤቆስጤዎችም፡ በዚህ ጊዜ ላይ፡ እጅ-ለ-እጅ ተያይዘን፡ "ጌታ ሆይ ኃይል ላክልን፡" ብለን አብረነው በመሆን ፈንታ፡ ብዙዎቹ ተቃወሙት። አያችሁ፡ እኛ ያለንበት ሁኔታ ይህ ነው፡ ርስት ሊሰጥ የማይቻልበት።

204 ኤፍሬም መቆየት አይፈልግም። አንዱ ወደዚህ ሲሄድ፡ ምናሴም ወደዚያ ሂዶ፦ "ኦህ፣ ጌታዬ ጥሩ የበቆሎ እርሻ ሰጠኝ!" ይላል፤ ጋድም፡ ወደዚህ በኩል ይመጣና፡ እንዲህ ይላል፦ "እሺ፡ ዘንድሮ፡ ቆይ ብቻ። እጃ መዝራት እንዳለብኝ አውቃለሁ፡ ነገር ግን በቆሎም አመርታለሁ። ሀሌ ሉያ!" አያችሁ? ከበቆሎ ጋር ምንም ጉዳይ የለህም፡ አጃህን አምርት፣ ድርሻህ አጃን ማምረት ነው። ከብቶችን ማሰማራት ሲገባችሁ በግ ማሰማራት የለባችሁም። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ርስት መስጠት ይፈልጋል። እያንዳንዳቸው ግን ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ይፈልጋሉ። "ሃሌ ሉያ!" አድርግ ብላችሁ ምንም ልትነግሯቸው አትችሉም። አይ፡ አይሆንም። አሁንም ያንን የፍየል ባህርይ እንደተላበሱ ናቸው፦ "በእ፣ በእ፣ በእ፣ በእ፣ በእ፣ በእ፣ በእ።" አየህ፡ ልትነግራቸው አትችልም። ትክክል ነው። አሁንስ፣ ያ እውነት አይደለም? ቤተ ክርስትያኒቱንም ርስቷን ማስያዝ አይቻልም። አየህ?

205 ቤተ ክርስትያን ወደ ልጅነት መብት አስቀድማ የተወሰነች መሆን ሲገባት፡ ይህ ማለት… እግዚአብሔር አንድን ሰው ወስዶ የገዛ ልጁ በማድረግ፡ አንድን ነገር መስጠት ማለት ነው። በመጀመሪያ፡ ያንን መርምሩትና፡ ትክክል ከሆነ እዩት። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስን መርምሩ ይላል። አንድ ሰው እንዲህ ነኝ ካለ፡ መርምራችሁ እውነቱን እወቁ። ትክክለኛ ነገር ከሆነ፡ አብራችሁ ሁኑ። ከዛ በኋላ ቀጥሉበት አታቁሙት "ጌታ ሆይ፡ ተጨማሪ ነገር ላክልን፡" በሉት። እያንዳንዱ ሰው ቦታውን እስኪይዝ ድረስ፡ ሂዱ፡ ቀጥሉ። ከዛ በኋላ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን ሰፍራ ሰፍራዋን ስትይዝ ታዩአታላችሁ። ያኔ ነው ፍልሰጤማውያንም የሚገዙላችሁ። አጫጭር ልብሶች ይቀራሉ፣ ጸጉር ያድጋል፣ ፊት ይጸዳል፣ ትንባሆ ይቀራል። አዎን። ሐናንያ እና ሰጺራ እና ጥቂቶች ባሉበት ሁኔታ፡

ቤተክርስቲያን ወደ ኃያል ኃይሏ መግባት ትጀምራለች። አዎን፡ ጌታዬ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በኃይሉ አንድ ላይ ስትቆም፣ ርስታቸውን እንዳገኙ እንደ እግዚአብሔር ልጆች፣ የእግዚአብሔር ልጅነት ቤተሰብ ርስት የተቀበለች፣ ክብር ያላት ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ሆና ስትቆም ታያላችሁ። አቤት፡ እሱ እየመጣ ያለው ለዚህ ነው።

206 ወንድሞች ሆይ ምን ያህል እንደራቅን ተመልከቱ? በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ላይ እንኳን መሰብሰብ አትችሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ የውሃ ጥምቀትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መሆኑን፡ ማየት የማይችል ማንኛውም ሰው፡ የትኛውም ሰው፣ ዓይነ ስውር ነው ወይም አእምሮው የጎደለው ነው። በትክክል። ትልቁ ውጊያም እዚህ ላይ ነው።

207 እስኪ—በመጽሀፍ ቅዱስ ወስጥ በአዲስቷ ቤተ ክርስትያን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጥምቀት በቀር፡ በሌላ ስም የተጠመቀ ሰው መኖሩን ሊያሳየኝ የሚችል አንድ ሰው ካለ ያሳየኝ። ስለዚህ፡ በሌላ መንገድ የተጠመቀ ሰው ካለ፡ መንፈስ ቅዱስን ያገኛ ዘንድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጠመቅ ዘንድ አለው። ናና አሳየኝ። እንደዚህ አይነት ነገር የለም። እንደዚህ ያለ ተልዕኮ የለም። ኢየሱስ በዚያ በተናገራቸው ጊዜ፦ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአባት በልጅ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፡ አስተምሯቸው ሲል፡" አባት ይሁን፣ ልጅ፣ ወይም መንፈስ ቅዱስ፣ እንዳቸውም፡ ስም አይደሉም፡ ጴጥሮስም፡ ከአሰር ቀን በኋላ መጣና፡ እንዲህ አለ፦ "ንስሐ ግቡ፡ ኃጢያታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።" እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሁሉም ቦታ...

208 እናም አንዳንዶች፡ በሌላ መንገድ፡ ለንስሐ ብቻ፡ በዮሐንስ ጥምቀት የተጠመቁ ሰዎች ነበሩ። ጳውሎስ ግን "እንደገና መጠመቅ አለባችሁ። ዳግም መመለስ አለባችሁ፡" አላቸው።

209 "ኧረ፡ እኛ'ኮ በታላቁ ቅዱስ ሰው በዮሃንስ እጅ የተጠመቅን ሰዎች ነን። ኢየሱስን ያጠመቀ ሰው'ኮ ነው።"

210 "እንግዲህ፡ ወንጌሉ ይህ ነው። ለእኔም የተገለጠው የእግዚአብሄር መንፈስ ይህ ነው። እኔ የጌታ ሐዋርያ ነኝ፣ ስለዚህ ከሰማይ መልአክ መጥቶ ሌላ ነገር ቢሰብክ... "

211 እስቲ ላንብበው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "መልአክ ወርዶ-... " ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ "መልአክ ከሰማይ መጥቶ ሌላ ነገር ቢናገር፣" ኤጲስ ቆጶስ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ የበላይ ጠባቂ፣ ምንም ቢሆን፣ "እኔ ከሰበክሁላችሁ ስብከት ሌላ ምንም ቢሰብክ የተረገመ ይሁን።" የለም... እንደዚህ አይነት ልማዶች የሉንም። አይ፡ ጌታዬ። ዝም በሉ... እንደዚህ ያለ ነገር የለም። እናንተ፡ እኛ... ከዛ በኋላም—እያችሁ፡ ሰዎች፡ ይሄን ለምን ማየት ያቅታቸዋል? ለምንድነው ሰዎች ይሄን ማ—ማ—ማመን የሚያቅታቸው? [አንድ ወንድም "አስቀድሞ መወሰን፡" ብሎ ተናገረ።—እርታዒ።] እያችሁ? አንድን ሰው አገኘው፡ ጂን። "አስቀድሞ መወሰን፡" ትክክል ነው። ለምን? "አብ የሰጠኝ ሁሉ" (ምን ይሆናል?) "ወደ እኔ ይመጣል።" ምንኛ እውነት ነው! "አብ የሰጠኝ ሁሉ ይመጣል—ወደ እኔ ይመጣል።" ምን ሆኜ ነው፡ ሌላ ጋር እየፈለግኩ ያለሁት? አገኘሁት። በጣም ጥሩ።

212 ይህን ጥቅስ ላንብብ እና ስለ ጳውሎስ ያለውን እነግራችኋለሁ፣ እሱ ያላቸው ነገሮች… እኔም ዛሬ ማታ እየሰበክሁት ያለውን መልዕክት፡ ጳውሎስ ስለ አስቀድሞ መወሰን፣ ስለ ጥምቀት በኢየሱስ ስም፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ ስለ ቤተ ክርስትያን ስርዓት፣ ወዘተረፈ ያስተማረው ይሄ ነው። እንዲህ አለ፦

> (ስለ ገላትያ ሰዎች ሲናገር) ወደ **ክርስቶስ ጸጋ**… **ከጠራችሁ ከእርሱ ዘንድ እንዴት ፈጥናችሁ እንደ** ተለያችሁ **እደነቃለሁ** (በሌላ አነጋገር፣ እጅግ አፍሬባችኋለሁ፡ ከዚያ ወደ ሌላ ፈቀቅ የሚያደርጋችሁ ሰው፡ እንዲገባባችሁ ፈቀዳችሁ።) **ወደ ሌላ ወንጌል፤**
>
> **እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ፡ የክርስቶስንም ወንጌል** ሊያጣምሙ፡ እውነተኛውን **የክርስቶስ ወንጌል** ሊያጣምሙ **የሚወዱ እንዳንዶች አሉ እንጂ።**

213 ተመልከቱ። አሁን፣ አስታውሱ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያልተጠመቁትን ሁሉ በድጋሚ መጥተው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንዲጠመቁ ያስገደደው ጳውሎስ ነው። እውነት እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? እነዚህ ምሥጢሮች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ተሰውረው እንደነበሩ እና አሁን ግን ለእርሱ ልጆች እነሆን ዘንድ፡ አስቀድመን የተወሰንን እንደነበርን፡ ለሱ እንደተገለጠለት የተናገረው ጳውሎስ መሆኑ፣ ስንቶች ታውቃላችሁ? የተናገረውን እዚህ ተመልከቱ፤

> **ነገር ግን እኛ ብንሆን፡ ወይም ከሰማይ መልአክ፡ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፡ የተረገመ ይሁን።**

214 "እኔ በዚህ አልስማማም፡ ጌታዬ፡" አትበል። የተረገመ ይሁን። ቀጣይ ጥቅስ ላንብበው፤

> **አስቀድመን እንዳልን፡ እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፡** አስቀድመን **ከተቀበልነው ወንጌል የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ፡ የተረገመ ይሁን።**

215 እውነት ነው። ወንድም፡ እና እህቶቼ ሆይ፡ የበቀደም ለታ ነገር፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከነበረ፤ ማለት በጥቂቱ እንዳየው ፈልጎ የወሰደኝ፡ ይሄን ስናገር ድፍረት እንዳይሆንብኝ ተስፋ አደርጋለሁ… አሁን፡ ደስ ደስ ብሎኛ፡ ደስ ደስ ብሎኛ ሳይሆን፡ በሰብከቱ ተባርኬአለሁ። እራሴን በራሴ ጎን አገኘሁት እንደ ደከማችሁ እና እንቅልፍ እንቅልፍ እንዳላችሁ እያወቅኩ አቆየኋችሁ። ይሁን እንጂ፡ ኦህ፡ እኔ… እናንተ—ራሳችሁ ወደዚያ እንድትሄዱ ምን ያህል እንደምመኝ ብታውቁልኝ ኖሮ! አያችሁ? እኔ፡ እንደገና ከጠየቅኩት በኋላ፡ እኔ… ሲጠይቀኝ ጊዜ… ያልኩት፦ "ምናልባት… "

"መጨረሻው ምን እንደሚመስል ማየት ትፈልጋለህ? " አለኝ፤

216 ዞር ብዬ ባየሁ ጊዜ አልጋው ላይ እራሴን ተጋድሞ አየሁት። እውነቱን ብቻ—እንደምናገራችሁ—ከብዙ ጊዜ በፊት ጀምራችሁ በእውነት ታውቁኛላችሁ። ሳሙኤል ሳኦልን ከመቀባቱ በፊት እንደ ተናገራቸው፡ አንድ

ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ፡ እውነት ከሆነው በቀር በጌታ ስም ሌላ ነገር ተናግሬአችሁ አውቃለሁን? ልክ ነው? ሁሉም እውነት ነበር። ገንዘብ ወይም ነዋይን ከእናንተ ፈልጌ ጠይቄአችሁ አውቃለሁን? በጭራሽ፡ አያችሁ፡ ጠይቄ አላውቅም። እናንተን ወደ ክርስቶስ መምራት ካልሆነ በቀር ሌላ ነገር አድርጌአችሁ አውቃለሁን? ትክክል።

217 ታውቃላችሁ፡ አሁን ሰዎች፡ ሜንታል ቴለፓቲስት ነው፣ ሱፐርስንስሪ ፐርሰፕሽኒስት ነው ሊሉኝ ይፈልጋሉ። እርግጥ፡ እነዚህ ነገሮች መነሳታቸው አይቀሬ ነው፡ መጽሀፍ ቅዱስም ይሆናል ብሏልና። ኢያንበሬስ እና ኢያኔስ ሙሴን እንደተቃወሙት፣ ወደ ዋናው መድረክ እስኪመጡ ድረስ፡ ሙሴ እንዳደረገው የሚመስል ብዙ ነገር አድርጓል። ትክክል ነው። ነገር ግን አስታውሱ፡ ኢያኒስ እና እያኔስ መፈወስ አልቻሉም። መፈወስ አይችሉም። መቅሰፍቶችን ማውረድ ችለዋል፡ መቅሰፍትን ማስወገድ ግን አልቻሉም። አያችሁ? በጣም ጥሩ። ለምን፡ እግዚአብሔር ፈዋሽ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው።

218 በፊታችሁ ታማኝ ለመሆን ሞክሬአለሁ። እውነቱን ለመናገርም ሞክሬአለሁ። በዚህ ፑልቢት ላይ... ለሰላሳ-አንድ አመታት ገደማ፡ ሰላሳ-አንድ አመታት ሙሉ፡ ሰወጣ እና ሰወርድ፡ ኖርኩ——ኑሬአለሁ፡ ምናልባት አንድ ቀን ይሄን ፑልቢት ትቼ ወደ ክብር እሄዳለሁ። ውድ ወዳጆቼ ሆይ፡ በዚያ ማዶ ሚስቴ፣ ሴት ልጄ፣ አባቴ፣ ወንድሜ፣ ሁሉም ተቀብረዋል። ሳጥኖቻቸው እና የተቀመጠላቸው ጉንጉን አበባ አይቻለሁ፡ አንድ ቀን እኔም፡ እጣዬ እንደሚሆን አውቃለሁ። እንግዲህ፡ እውነት ነው። ነገር ግን በቅንነት፣ በሙሉ ልቤ፣ በሙሉ ልቤ እነግራችኋለሁ፣ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛው ወንጌል እንደ ሰበክሁላችሁ ግን አምናለሁ። እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ እንዳለባችሁ፣ ሁላችሁ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት፡ መቀበል እንዳለባችሁ አምናለሁ። ይህን ስትፈጽሙ፡ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ በጎነት፣ ትህትና፣ ጨዋነት፣ ትዕግስትን፣ እምነትን ያፈራላችኋል።

219 እና በቀደም ለት ማለዳ፡ የገጠመኝ ነገር፡ አላውቀውም። እኔ እዚህ ሰውነቴ ላይ ሆኜ ራዕይን እንዳየሁ፣ ወይም ከዚህ ተወሰጄ እንደሆነ፣ መናገር አልችልም። አላውቅም፡ ይሄ ነው ማለት አልችልም። ብቻ እኔ የማውቀው፡ ሞት——ያቺ ትንሿ መውጊያ፡ አፈራት እንደነበረ ነው። በርግጥ ፍርኃት አይደለም ኢየሱስም ባልመጣልኝ ነበር፡ አሁን፡ አልፈራም፡ ምክንያቱ አሁን——አያስፈራኝም፤ ምናልባት ግን አየር ላይ ዝም ብሎ እንደሚበር ጭጋግ የማገኛችሁ ቢሆን ኖሮ። አሁን ግን አይቼዋለሁ። ሰዎቹ ባየኋቸው ጊዜ፡ ትክክለኛ ሰዎች ናቸው። ሰዎቹም በምድር በነበሩ ጊዜ ከእኔ ጋር ዝምድና የነበራቸው ሰዎች ናቸው፡ የመጀመርያዋ ሚስቴም ሳይቀር ነበረች። በዚያ ግን እህቴ እንጂ፡ ሚስቴ አልነበረችም። ውድ ወንድሜ እያለች ጠራችኝ እንጂ፡ ባሌ አላለችኝም። ምንም አይነት ፍትወት፡ ወይም መሰል ስሜት አልነበረም፡ ሊሆንም አይችልም፡ ፍጹም የሆነ፡ እጅግ የሚያስደስት፡ ፍጽምና ነበር።

ጥያቄ ሆኖብኛል፡ እኔ አላውቅም፡ ጥያቄ ሆኖብኛል፤ ምድርን ለቃ ከመሄድዋ በፊት፡ ያየችው ነገር ይህ ይሆንን? ያኔ በዚያ በሆስፒታሉ፡ በጠራኋት ጊዜ፡ እንዲህ ብላኝ ነበር፦ "ቢሊ፡ ሰብከኸዋል፡ ስለሱም ተናግረኻል፡ ይሁን እንጂ፡" አለችኝ፦ "ምን እንደሆነ አታውቀውም።" "የመቆየት ፍላጎት የለኝም፡" አለችኝ።

220 በተለያዩ የዓለም አገራት አብሮኝ የሰበከው፣ በዚህ ፑልቢት ያገለገለው ሽማግሌ፡ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው፡ ኤፍ. ኤፍ. ቦሰዎርዝ፡ የእሱም እንዲህ ይሆን ወይ ብዬ አስባለሁ። ቅዱስ ሽማግሌ፡ የእግዚአብሔር ሰው፡ ኤፍ. ኤፍ. ቦሰዎርዝ፡ ሁላችሁም፡ በሚባል ደረጃ፡ ታውቁታላችሁ። ከሁለት ሰዓታት በፊት፡ ማለቴ፡ ከማለፉ ከአንድ ከሁለት ሳምንት በፊት፡ ልጠይቀው ሄድኩና፡ የዘጠና ዓመት ሽማግሌ፡ አልጋው ላይ በጀርባው ተኝቶ አገኘሁት። ያረጁ እጆቹ አንሰቶ፡ መላጣውን ጭንቅላቱ እና ፊቱ ላይ ያለውን ጢሙን ያሻሻል። ሽማግሌውን በክንዴ ላይ ደግፌ ያዝኩትና ጮኽ ብዬ፡- "አባቴ፡ አባቴ፡ የእሰራኤል ሰረገሎችና ፈረሰኞች" አልኩ።

ጴንጤቆሰጤን የሚወክል፡ እና እውነተኛ ሐዋርያ የሆነ ሰው አለ ከተባለ፣ ኤፍ. ኤፍ. ቦሰዎርዝ ነው ንጹሕ፣ ቅን፣ ባለ እውነተኛ ወንጌል፣ ማለት፡ ቦሰዎርዝ ነው። እና በክንዴ ደግፌው፡ "አባቴ፡ አባቴ፡ የእሰራኤል ሰረገሎችና ፈረሰኞች፡" ባልኩ ጊዜ።

221 "ልጄ ሆይ፡ በወንጌል ሰራ ጸንተህ ቁም፡" አለኝ። አለኝም፡- "ከቻልክ፡ ወግ አጥባቂዎች ከመቅደማቸው በፊት፡ አንዳንድ ወጣቶችን ወደ ውጭ አገር ይሂዱ ላካቸው። ልጄ ሆይ፡ በአንተ ያለውን እውነተኛው ወንጌል ይዘው ይሂዱ።" "አገልግሎትህ ወደተጠራበት ሰፍራ መጓዝ ገና አልጀመረም፡" አለኝ። "አንተ ብራንድ ኒው ብራንሃም ነህ፡" አለኝ። "ልጄ ሆይ፡ ገና ወጣት ነህ፡" አለኝ።

"ወንድም ቦሰዎርዝ፣ አርባ ሰምንት ዓመቴ'ኮ ነው፡" አልኩት።

222 "ገና አልጀመርክም፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ፡- "ግብህ ሳትመታ፡ የጴንጤቆሰጤ ወጣት ሰባኪዎች ከንቱ ነገር ይዘው፡ አገሪቷን እና—መላ ዲፕሎማቶችን በማነሳሳት ነገሩን እንዲመርዙ አትፍቀድ።" "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የተቀበልከውን ወንጌል ይዘህ፡ ቀጥል፡" አለኝ። "የአምላካችን ሐዋርያ ወይም ነቢይ እንደሆንክ እኔ—አምናለሁ፡" አለኝ።

223 አየሁትና፣ በክንዴ እቅፍ አደረግኩት። እና ጠየቅኩት፡- "ወንድም ቦሰዎርዝ፣ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። ካገለገልክባቸው ዓመታት ሁሉ... እጅግ ልዩ የሆነችና... የተደሰትክባት ቀን መቼ ናት ብዬ ጠየቅኩት? "

"አሁን ናት፣ ወንድም ብራንሃም፡" አለኝ።

"እየሞትክ እንደሆነ አውቅሃልን? " አልኩት፤

"እኔ አልሞትም፡" አለኝ።

"ምን... ደሰተኛ ጊዜዬ አሁን ናት ለምን አልክ? " ብዬ ጠየቅኩት፤

224 እነሰ ያሉች በር በዚያ ነበረችና። እንዲህ አለኝ፡- "አሁን ፊቴን ወደዚያች በር አዙሬ እዚህ ተኝቻለሁ። በሕይወቴ... በዘመኔ ሁሉ የቆምኩለትን፡ እና የሰበኩትን፡ የምወደው ውዴ፡ በማንኛውም ደቂቃ፡ ወደዚህች በር ይመጣል፡ እኔም አብሬው እሄዳለሁ።" ትኩር ብዬ አየሁት፡ አብርሃምን፣ ይሰሐቅን፣ እና ያዕቆብን ያየሁ ያክል—ተሰማኝ፡ ብዬ አሰብኩ።

225 እጁን ያዝኩኝና፡ እንዲህ አልኩት፡- "ወንድም ቦሰዎርዝ፣ ሁለታችንም አንድ አምላክ እናምናለን፣ አንድ አይነት ነገር እናምናለን። የመጨረሻዋ ትንፋሽ ከሰውነቴ እሰክትወጣ ድረሰ በእግዚአብሔር ጸጋ እሰብካለሁ። ባለኝ አቅም ሁሉ ለእግዚአብሔር ታማኝ እሆናለሁ። ከማንም ጋር ወይም በማንኛውም

አይነት ሁኔታ በወንጌል አልደራደርም። በቻልኩት ያህል ለእግዚአብሔር ታማኝ እሆናለሁ። ወንድም ቦስዎርዝ፡ ከአሁን በኋላ ወጣት እንጂ፡ ታዳጊ... ወይም ሽማግሌ በማትሆንባት በተሻለች ምድር አገኝሃለሁ።"

226 "ወንድም ብራንሃም፡ አታስብ፡ አንተም ትገባባታለህ፡" አለኝ።

227 ከሁለት ወራት በኋላ... ከመሞቱ ከአንድ ከሁለት ሰዓታት በፊት፡ ያን ቀን ይሞታል ብዬ ስላሰብኩ፡ ሚስቴም፡ (እሷን ሁሌ ያሰባታል)፡ እሱን እና ወይዘሮ. ቦስዎርዝን፡ ልትጠይቃቸው ገባች። ለሁለት ሰዓታት ያክል፡ ተኝቶ ነበር። አይኑን ገልጦ አየ፡ እና ከአልጋው ዘሎ ተነሳና፡ በእግሮቹ ቆመ። እንዲህ አለ፦ "እናቴ፡ እንደው፡ ለብዙ አመታት አላየሁሽም! አባቴ! ወንድም ጂም፡ ሰማ፡" አለው፡ "አስታወስክ፡ በጆሌት፡ ኤሊኖስ፡ ጌታ ካስቀበልኳቸው ሰዎች መካከል አንዱ አንተ ነህ።" ከሞተ'ኮ ሐምሳ አመት ሆኖታል። አያችሁ? እንዲህ አለ፦ አዎን! "አንቺ እህት **እከሊት-እና-እከሊት** ነሽ። አዎን፡ ጌታን ያስቀበልኩሽ—በዊኒፔግ በነበረው ጉባኤ ነው። አዎን። አየሽ፡ ያቻትና እህት **እከሊት-እና-እከሊት።** ቆይቷል ካየሁሽ... አዎን፡ ጌታን የተቀበልሽው፡ **እንትና-እና-እንትና** በተባለ ሰፍራ ነበር።" ለሁለት ተከታታይ ሰዓታት ወደ ጌታ ከመራቸው ጋር ሰላምታ ተለዋወጠ። ወደ ቦታው ተመለሰ፣ እና ተኛ፣ እጆቹን አጣመረ፣ እና ፍጻሜው ያ ነበር። ወንድም ኤፍ. ኤፍ. ቦስዎርዝ ኢየሱስ በቀድሞ ምሽት ወዳሳየኝ ወደዚያ ምድር ገብቷልን? ገብቶ ከሆነ፡ ዛሬ ወጣት ሰው ሆኖ በዚያ አለ። ጌታ ነፍሱን ያሳርፍ። እኔም ወደዚያች ምድር መግባት እችል ዘንድ በታማኝነት መኖር ይሁንልኝ። የክርስቶስ—እውነተኛ ባርያ ያድርገኝ!

228 በሕይወቴ አፈርኩ። አፍሬአለሁ... እ—እ... እንደው በፊታችሁ በሐጥያት በድያችሁ ከሆነ፡ ኑ—ኑና ንገሩኝ። አያችሁ? እግዚአብሄር በጸጋው እንድሰራለት ባደረገኝ ነገሮች ሁሉ ላይ በትክክል ለመኳዝ ጥሬአለሁ። አያችሁ? አያችሁ? ነገር ግን፣ ተመልከቱ፣ ጓደኞቼ፣ በህይወቴ ውስጥ የምታውቁ የሆነ ነገር ካለ የእናንተ እዳ አለብኝ፣ ኑና ንገሩኝ። አሁንም፡ ተመልከቱ፡ ወንጌል ለእናንተ ለመሰበክ ባለ እዳ ነኝ። በዚያ ወዲያ ማዶ ከአድማስ ባሻገር፡ የእያንዳንዳችሁ ወጣት ወንዶች፣ እና ሴቶች ፊት ማየት እጠብቃለሁ፣ እዳ አለብኝ። አሁን እናንተ ባላችሁበት እና በቦታው መካከል የአንድ ትንፋሽ ርቀት ብቻ ነው። ይህ፡ እውነት ነው። ቅርብ ነው።

229 አሁንም በመፈናፈስ ሳይሆን በአክብሮት እላለሁ፡ የጸጋው ሁሉ አምላክ፣ የሰማይ አምላክ፣ "ባባ፡" ወደዚህ ተመልሰን ምድራዊ ሰውነታችንን በምንቀበልበት በዚያ በታላቅ ቀን፣ ከምድሪቱ ፍሬ እና ከወይን እንበላለን፣ እንጠጣለን። "ቤቶችን ይሠራሉ ሌላ ሰው አይኖርበትም። ወይን ይተክላሉ ሌላ አይበላውም።" አያችሁ? አንድ ሰው ወይን ሲተክል፣ ልጁ ይወርሰዋል፣ የእሱም ልጅ ይወርሰዋል፣ ይቀጥላል። በዚያ ግን እንዲህ አይደለም፡ ይተክላል እሱም ይቆያል። አያችሁ፡ ይህ እውነት ነው። ለዘለአለም በዚያ እንሆናለን። በምድሪቱ ውስጥ፡ ሁላችሁም፡ ያሳየኝ።

230 የምናገረው ነገር ለስላሴ አገልጋዮች እንኳን እንደሆነ አውቃለሁ። ወንድሞቼ ሆይ፣ ይህን ሰናገር—ይህን የተናገርኩት፡ እናንተን ለመጉዳት አይደለም። እኔም፡ በሦላሴ አምናለሁና፡ በሶስት አማልክት ሳይሆን፡ በእግዚአብሄር ሶስት መገለጫዎች (አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ)፡

በሰላሴ እምናለሁ። ገባችሁ? ሶስት መገለጫዎች እንዳሉ፡ በሙሉ ልቤ፡ በትክክል እምናለሁ፡ "አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ፡" ሶስት አማልክት ግን አይደሉም። የእግዚአብሄር ሶስት መገለጫዎች-... ወይም አሰራር ናቸው። እግዚአብሔር አንድ ጊዜ በአባትነት፣ በልጅነት መልክ ኖሯል፣ አሁን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አለ። አንዱ አምላክ በሶስት አሰራር። እነዚህም...

231 አባት፣ ልጅ፣ እና መንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚ አብሔር ስም አይደለም። እግዚአብሄር አንድ ስም አለው፡ ስሙም ኢየሱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ "በሰማይ እና በምድር ያለው፡ የእግዚአብሔር ቤተሰብ በሙሉ ኢየሱስ ይባላል።" ትክክል ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር፡ አንድ የሰው ስም ነበረው። እግዚአብሔር... ጆሆቫ-ጂረህ፣ ጂሆቫ-ራፋ የሚባልባቸው ሰሞች ነበሩት፡ እነዚህ የአምላክነቱ የመዓርግ ሰሞች ናቸው። ሰሙ ግን አንድ ናት፡ ኢየሱስ! እርሱም ይህ ነው።

232 እና በእውነት፡ ወንድሞቼ ሆይ፡ ከእኔ ጋር ባትስማሙም፣ አስታውሱ፡ ለማንኛውም፡ በዚያ—እ—እገኛችኋለሁ። አያችሁ? አብሬአችሁ በዚያ እገኛለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እወዳችኋለሁ።

233 እና ቤተ ክርሰቲያንን ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡ እሁድ ጠዋት ከዚህ እንገናኛለን ከሰዓትም ጉባኤ እንዲኖረን፡ ከሁለት ሰዓታት በላይ እንዳላዘገያችሁ እሞክራለሁ፡ ከቻልን፡ እና ዛሬ ማታ እንዳደረኩት ባደርግ፡ አሰር-ሰላሳ። ይቅር ትሉኛላችሁ? ወዳጆቼ፡ የኔ ማር፡ ጊዜ የለንም። ማር ስለሆናችሁ "የኔ ማር" ብዬ—ጠራኋችሁ። ለእኔ—ማሮቼ ናችሁና። ትታውቃላችሁ? አንድ ቃል... ላሳያችሁ። ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ "(ቤተ ክርሰትያኑን) ለአንድ ወንድ አጭቻቸዋለሁና በእግዚአብሄር ቅንዓት፡ እቀናላችኋለሁ አላቸው።" ይሄውላችሁ፡ ገባችሁ። ይሄ ነው። "እንደ ንጽሕት ድንግል፡ ለክርሰቶስ፡ አጭቻቿለሁ።"

234 ስለዚህ፡ ያኔ የተናገረው፡ እውነት ከነበረ... ሰዎቹም፡ ሲናገሩ፡ እንዲህ አሉ፡ "ኢየሱስ ወደ አንተ ይመጣል፡ አንተም ወደ እርሱ ታቀርበናለህ፡" እንደ ንጽሕት ድንግል። "በሰበክሃቸው ቃል ትፈረዳለህ።" እነሆም፡ እኔ፡ ጳውሎስ ለቤተ ክርሰቲያኑ የሰበከላትን እኔ ብሰብክላችሁ፡ የእሱ ቡድን ከገባች፡ ተመሳሳይ ስለሆንን፡ የእኛም ትገባለች። አሜን።

አሁን "እግዚአብሄር ይባርካችሁ፡" ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። አሁን... ? ... ለተወደደው ፓስተራችን፡ ወንድምም ነቪለ።

**ማደጎ** 2 AMH60-0518

(Adoption 2)

**ማደጎ ተከታታይ ስብከት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሮብ ማታ፣ ግንቦት 18 ቀን፣ 1960፣ በጀፈርሰንቪል፣ ኢንዲያና፣ በዩ.ኤስ.ኤ. ከሚገኘው ብራንሃም ተበርናል፣ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org